ገለባ ክሶች

በተለያዩ ጊዜያት ሚሽነሪዎች ኢስላም ላይ ላቀረቧቸው ትችቶች የተሰጠ ምላሽ!!

ክፍል - ፩

ዝግጅት
አቡ ዩሰራ
ያህያ ኢብኑ ኑህ

ማውጫ

ከሰማይና ከምድር ቀድሞ የተፈጠረው ማነው?.....3
የመጀመሪያ ሙስሊም ማን ነው? 5
ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) "በእኔ ምን እንደሚሰራ አላውቅም" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?.....7
እውን ቁርአን የተሟላ አይደለምን? 10
በኦሪትና በወንጌል ፍረዱ? 13
መዳን በኢስላም እንዴት ነው? 16
እውን አላህ ሰዎችን ያጠማልን? 17
እውን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሀጥያትን ሰርተዋልን? 23
ሰይጣን ምን አጠፋ? 28
ቁርአን የመፅሀፍ ቅዱስን አረጋጋጭ ነዉን? 31
እውን ቁርአን ጠጅ ይፈቅዳልን? 33
ቁርአን ለምን ማርያምን የአሮን እህት ሆይ ብሎ ይጠራታል? 36
እንዴት በገነት ዉስጥ ጠጅ ይኖራል? 40
አጋሪዎችን ግደሉ? 42

ከሰማይና ከምድር ቀድሞ የተፈጠረው ማነው?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ አዛኝ በሆነው!!!

አብዛኛውን ሰው የተጋጨ የሚመስለው ነጥብ ይህ ከላይ በርዕሱ ያስቀመጥኩት ጉዳይ ነው፡፡አንቀጾችን እናስቀመጥና እንድ ባንድ ለማየት እንሞክራን፡፡

ምድር ቀድማ ተፈጥራለች ለሚለው ሀሳብ የሚቀርበው የቁርአን አንቀጽ 2፡29

«««[٢:٢٩] هُوَ الَّذِي خَلَقَ لَكُم مَّا فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا ثُمَّ اسْتَوَىٰ إِلَى السَّمَاءِ فَسَوَّاهُنَّ سَبْعَ سَمَاوَاتٍ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ

‹‹እርሱ ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለእናንተ የፈጠረ ነው፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ፤ ሰባት ሰማያትም አደረጋቸው፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡

ሰማይ ቀድማ ተፈጥራለች ለሚለው ደግሞ 79፡27

«ባፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይንስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት፡፡ ከፍታዋን አጓነፀ፤ አስተካከላትም፡፡ ሌሊቷንም አጨለመ፡፡ ቀንዋንም ገለጸ፡፡ ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት፡፡›› 79፡27-30

ይህ ጥያቄ በሁለት መከራከሪያ ነጥቦች መመለስ ይቻላል፡፡

ቀዳሚ መከራከሪያ ነጥብ

የመጀመሪያው አንቀጽ ማለትም 2፡29 ምድርን አስመልክቶ የተጠቀመው ቃል ኸለቀ የሚል ነው፡፡ ትርጓሜውም ፈጠረ ማለት ነው፡፡ይህ ማስገኘትን የሚገልጽ ነው፡፡ ወደ ሁለተኛው አንቀጽ ስንመጣ ግን ማለትም 79፡27-30 ምድርን አስመልክቶ የሚጠቀመው ቃል «ደሀሀ» የሚል ነው፡፡ ትርጓሜውም መፈጠርን ሳይሆን የሚገልጸው ዘረጋት-አስዋባት-አሳመራት የሚል ትርጓሜን ይሰጣል፡፡ግዙፉን የአረብኛ ዲክሽነሪ ሊሳኑል አረብን መመልከት ይቻላል፡፡ይህም ምድርን ስለመፍጠር ሳይሆን የሚገልጸው ከተፈጠረች በኋላ ስለተደረጉ ፊቸሪንግ ወይንም የማሳመር ስራዎች ነው፡፡ እነኝህም የሚፈልቁ ምንጮችን ማድረግ፣ጋራዎችን ማደላደል ወዘተ ማለት ነው፡፡ ይህንን ለመረዳት ቀጥሎ ያሉትን አንቀጾች ማየት በቂ ነው፡፡

«ውሃዋንና ግጦሿን ከእርሷ አወጣ፡፡ ጋራዎችንም አደላደላቸው፡፡ለእናንተና ለእንስሶቻችሁ መጣቀሚያ ይኾን ዘንድ (ይህን አደረገ)፡፡ ›› 79፡31-33

ሁለተኛ መከራከሪያ ነጥብ

ከቃላት አጠቃቀም አንጻር ‹ሱመ› (ከዚያም) የሚለው ቃል በአረብኛ የቋንቋ አጠቃቀም የጊዜ ቅደም ተከተልን ብቻ አይገልጽም፡፡ይህ ቃል መጣ ማለት የግድ አንዱ ተግባር ከሌላው ተግባር ያለውን የጊዜ ቅደም ተከተል ይገልጻል ማለት ብቻ አይደለም፡፡ በአረብኛ ሰዋሰው መሰረት ‹ሱመ. የሚለው ቃል «በተጨማሪም» ወይንም /moreover/ ለሚለው ቃል በትርጓሜነት ያገለግላል፡፡ ማስረጃውን በምስሌ በምሳሌ ማስቀመጥ እንችላለን፡፡

««ይህም ቀጥተኛ ሲኾን መንገዴ ነው፤ ተከተሉትም፡፡ (የጥመት) መንገዶችንም አትከተሉ፡፡ ከ(ቀጥተኛው) መንገዱ እናንተን ይለያዩዋችኋልና፡፡እነሆ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ፡፡#ከዚያም ለሙሳ በዚያ መልካም በሠራው ላይ (ጸጋችንን)

ለማሟላት ነገርንም ሁሉ ለመዘርዘር መጽሐፉን (ለእስራኤል ልጆች) መሪና እዝነት ይኾን ዘንድ ሰጠነው፡፡ እነርሱ በጌታቸው መገናኘት ሊያምኑ ይከጀላልና፡፡>> 6:153

ቀጥተኛው መንገዴ የተባለው ቁርአን ሲሆን እዚህ ጋ አላህ(ሱ.ወ) ስለቁርአን ከገለጸ በኋላ በ‹ሱመ› አያያዥነት ተውራትን አስከትሎ ገለጸ፡፡ ስለዚህ የጊዜ ቅደም ተከተል ቢሆን ኖሮ ከሱመ በፊት ቁርአን ሳይሆን መገለጽ የነበረበት ተውራት ነበር፡፡ ግን ሱመ እዚህ ጋር ለመግለጽ ስለነበር አገልግሎቷ ከቁርአን በኋላ ተገለጸች፡፡ ለዚህ እጅግ በጣም ብዙ የአረብኛ ሰዋሰው መጽሀፍትን በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ለአብነት ያክል አንዱን ልጥቀስ

"Written Arabic - An Approach to the Basic Structures" by A.F.L. Beeston (cost about $25.00), Chapter 3, note 22.

ማጠቃለያ

በአጭሩ ቅደም ተከተሉ ሲተነተን በመጀመሪያ ምድር ተፈጠረች ነገር ግን አሁን ባለንበት መልኩ የተዘረጋች አልነበረችም፡፡ ከዚያም ቀጥሎ ሰማይ ተፈጠረች ከሰማይ መፈጠር በኋላ ምድር ተዘረጋች በዚህ መልኩ ውሃዋንና ግጦሿን ከእርሷ አወጣ፡፡ ጋራዎችም ተደላደሉ፡፡(ተፍሲር ኢብን አባስ)

ምንጭ - ተፍሲር አድዋዕ አል በያን (10/16-18)

- Islam question and answer q-70217 Dr. Muhammed salih al-munajjid (ዌብሳይት)

ወሏሁ አእለም!!

የመጀመሪያ ሙስሊም ማን ነው?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው!!!!!

ይህ ጥያቄ አብዛኛውን ጊዜ ተጠይቆ ምላሽ የተሰጠበት ቢሆንም ተደጋግሞ ከመነሳቱ አንጻር ምላሹን ማቅረብ ስለሚኖርበት ኢንሻአላህ ከዚህ በታች መልሶችን ዘርዘር አድርጌ ለማንሳት እሞክራለሁ፡፡

በነኝህ ሰዎች ተደጋግሞ የሚነሳው ጥያቄ ታዲያ በብዙ ቦታዎች ላይ የተለያዩ ነብያት ሙስሊም እንደሆኑ ከተገለጸ በኋላ በሌላ ቦታ ደግሞ ነብዩ ሙሀመድ የመጀመሪያ ሙስሊም እንደሆኑ ይገልጻል ይህ አይጋጭም ወይ የሚል ነው፡፡

አዎ በርግጥም አይጋጭም፡፡ ተከተለኝማ!!!! አንቀጾችን ከታች ካስቀመጥን በኋላ ወደ ምላሹ እንዘልቃለን፡፡

ቁርአን ኢብራሂምን እስማኢልን ሙስሊም ይላቸዋል፡-

«ጌታችን ሆይ! ላነተ ታዛገሮችም አድርገን፡፡ ከዘሮቻችንም ላንተ ታዛገሮች ሕዝቦችን (አድርግ)፡፡ ሕግጋታችንንም አሳየን፤ (አሳውቀን)፡፡ በኛም ላይ ተመለስን፤ አንተ ጸጸትን ተቀባዩ ሩኅሩኅ አንተ ብቻ ነህና፡፡» (ሱረቱ አል-በቀራህ ምዕ.2 ቁ.128)

ያእቆብና ልጆቹ ሙስሊሞችም ሙስሊም መሆናቸውን ይገልጻል፡-

በርሷም (በሕግጋቲቱ) ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ፡፡ ያዕቁብም (እንደዚሁ ልጆቹን አዘዘ)፡፡ «ልጆቼ ሆይ! አላህ ለናንተ ሃይማኖትን መረጠ፤ ስለዚህ እናንተ ሙስሊሞች ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ» (አላቸው)፡፡(ሱረቱ አል-በቀራህ ምዕ.2 ቁ.132)

በተመሳሳይ እየሱስ እና ሐዋሪያቱ እንኳ ሙስሊሞች መሆናቸውን ይናገራል፡፡

ወደ ሐዋርያትም «በኔና በመልክተኛዬ እመኑ» በማለት ባዘዝኩ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ «አመንን፤ እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክር» አሉ፡፡(አል-ማኢዳ ምዕ.4 ቁ.111)

ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመጀመሪያ ሙስሊም እንደሆኑ የሚገልጽበት አንቀጽ ደግሞ

ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል፡፡ «ለእርሱ ተጋሪ የለውም፡፡ በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ፡፡ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)፡፡ (ሱረቱ አል-አንአም ምዕ.6 ቁ.162-163)

አሁን ወደ መልሱ እንዝለቅ!

በመጀመሪያ ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን እንመልከት፡-ኢስላም የሚለው ቃል ሁለት ትርጉሞች አሉት፡፡የመጀመሪያው እጅ መስጠት ያለ ተቃውሞ መታዘዝ የሚል ሲሆን በአረብኛው ኢስቲስላም ተብሎ ይጠራል፡፡ሁለተኛው ደግሞ ሰላም ማለት ነው ሲሆን በአጠቃላይ ኢስላም ማለት በአጭሩ ‹‹ለአላህ ያለ ተቃውሞ በመታዘዝ እጅ በመስጠት ሰላምን መጎናጸፍ ማለት ነው፡፡››

እስልምና ማለት ይህ መሆኑን ከተረዳን ሁሉም ነብያት ሙስሊሞች ነበሩ፡፡

ሁሉም ነብያት ለአላህ እጅ የሰጡ፤ለፈቃዱ ያደሩ፤ ትእዛዙን የተገበሩ በመሆናቸው በቁርአኑ አገላለጽ ‹‹ሙስሊሞች›› (ለአላህ ታዛዦች) ተሰኝተዋል፡፡ ኢብራሂም፤ ኢስማኢል፤ እየሱስ ሙሳ፤ የእየሱስ ሐዋሪያት፤ ዩሱፍና ሌሎችም በየዘመናቱ የነበሩ አማኞች ሁሉ ‹‹ሙስሊሞች›› የተባሉትም ከእዚህ አንጻር ነው፡፡ አምላክ ከጥንት ጀምሮ ለሰው ልጅ የመረጠው ሐይማኖትም እስልምና ብቻ ነው፡፡ እርሱም የአምላክን ትእዛዝ ያለ ተቃውሞ መሙላት ነው፡፡

ታዲያ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የመጀመሪያ ሙስሊም መሰኘታቸው ከምን አንጻር ነው ከተባለ የመጀመሪያነታቸው ከነበሩበት ማህበረሰብ አንጻር ነው የሚል ይሆናል፡፡

ተፍሲር ኢብን ከሲር ለአንቀጹ ማብራሪያ የሰጡትን ማብራያ ይመልከቱ፡፡ ለዚህ ንግግር ማስረጃው ምንድን ነው ከተባለ ሌሎችም ነብያቶች ተመሳሳይ ገለጻ ተጠቅመዋል የሚል ይሆናል፡፡

ለምሳሌ ሙሳ የአምላክን አንድ ታአምር ባዩ ጊዜ እንዲህ ብለዋል፡-

‘‘ሙሳም ለቀጠሯችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ፡- «ጌታዬ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ ወደ አንተ እመለከታለሁና» አለ፡፡ (አላህም)፡- «በፍጹም አታየኝም ግን ወደ ተራራው ተመልከት፡፡ በስፍራውም ቢረጋ በእርግጥ ታየኛለህ» አለው፡፡ ጌታው ለተራራው በተገለጸ ጊዜ እንኩትኩት አደረገው፡፡ ሙሳም ጮሆ ወደቀ፡፡ በአንሰራራም ጊዜ «ጥራት ይገባህ፡፡ ወዳንተ ተመለስኩ፡፡ እኔም (በወቅቱ) የምእምናን መጀመሪያ ነኝ» አለ፡፡’’ (ሱረቱ አል-አእራፍ ምዕ.7፡143)

ሙሳ ይህንን ቃል ሲጠቀም ከሱ በፊት የነበሩ ነብያት አነ ኑህ አብርሀምና ሌሎችም ነብያትና ምዕመናን አማኞች አይደሉም ለማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከሙሳ ህዝብ አንጻር አላህ እንደማይታይ ካረጋገጡና ካመኑ ሰዎች መካከል ሙሳ የመጀመሪያነታቸውን ነው የሚገልጸው፡፡ ይህ አገላለጽ ቁርአን ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ በማስረጃ እናድረገው፡፡

የፊርአውን ደጋሚዎችም እንዲህ ብለዋል፡-

«እኛ የምእምናን መጀመሪያ በመኾናችን ጌታችን ኀጢአቶቻችንን ለእኛ ሊምር እንከጅላለን፡፡» (ሱረቱ አል-ሹአራእ ምዕ.26፡51)

የፊርአውን ደጋሚዎች የመጀመሪያ አማኞች መሆናቸውን ሲገልጹ ሙሳንና ወገኖችን አማኞች አይደሉም እያሉ አይደለም ከፊርአውን ወገኖች መካከል የመጀመሪያዎቹ አማኞች መሆናቸው መግለጻቸው ነው ::

ስለዚህም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሌሎች ነብያት እምነት የሆነውን እስልምና የሰበኩ ቢሆንም ከነበሩበት ትውልድ አንጻር የመጀመሪያ ሙስሊም መሆናቸው ነው፡፡ አንቀጹ በአጭሩ ሲብራራ ይህን ይመስላል፡፡ ግጭት ተብለው የሚፎከርባቸው ትችቶች እንዲህ ሲፍታቱ በዚህ መልኩ ገለባዎች ናቸው፡፡

ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) "በእኔ ምን እንደሚሰራ አላውቅም" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

አብዛኛው ክርስቲያን ሚሽነሪዎች የቁርአን 46፡9 ን በመጥቀስ "ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ገነት ስለመግባታቸው ተጠራጣሪ ነበሩ" ሲሉ ይደመጣሉ ጹሁፎቻቸውን ከነግሳንጋሰቸውና ቡገራቸው የሚተረጉሙላቸው ሰዎች ደግሞ አንቀጾችን ማረጋገጥና ማመሳከር ሳያስፈልጋቸው እንደ ወረደ በአማርኛ ቋንቋ ተርጉመው ያስቀምጡታል፡፡ ከዚያም ይህንን ሚስኪን ክርስቲያን አማኝ ቁርአን ውስጥ ስህተት አገኘነልህ በማለት በአጉል ምኞት ጮቤ ያስረግጡታል፡፡ ከዚህ በፊት በተከታታይ ለእያንዳንዳቸው ምላሽ በመስጠት ከሶቹ ምን ያህል የወረዱና ውሀ የሚያነሱ እንዳልሆነ ተመልከተናል፡፡ ዛሬም እንደተለመደው በአላህ ፍቃድ አንቀጹን ከታች በማስቀመጥ ምላሹን እንሰጣለን!!!! መልካም ንባብ!!

አንቀጹ እንዲህ ይላል፡-

«ከመልከተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም፡፡ በእኔም በእናንተም ምን እንደሚሥሠራም

አላውቅም፡፡ ወደእኔ የሚወረደውን እንጅ ሌላን አልከተልም፡፡ እኔም ግልጽ አስፈራሪ እንጅ

ሌላ አይደለሁም» በላቸው፡፡» 46፡9

ክርስቲያን ሚሽነሪዎች ይህንን አንቀጽ በማስቀመጥ ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) በእሳቸው ምን እንደሚሰራ አላውቅም ማለታቸው ስለመጽደቃቸው እርግጠኛ አልነበሩም ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ አውነት አንቀጹ እነሱ እንደሚሉት ይህንን መልዕክት ያስተላልፋለን? ከታች ማስረጃዎችን እያነሳን ክሱን እንመዝናለን፡-

አንቀጹ በሚቀጥለው ህይወት ወይንም በየውመል ቂያማ አይደለም የሚያወራው፡፡ አንቀጹ የሚናገረው በዚህች ምድር ስለሚከሰቱ የወደ ፊት ጉዳዮች ለምሳሌ ህመምን ይመስል፡ ከሀገር ማስወጣትንና የተለያዩ ምድራዊ ጣጣዎችን አስመልከቶ ምን እንደሚገጥማቸው አያውቅም የሚል መልዕክት ነው ያለው፡፡ ተፍሲር አል-ጀላለይን ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፡-

Say: 'I am not a novelty, unprecedented, among the messengers, that is to say, [I am not] the first to be sent [by God as His Messenger]. Already many of them have come before me, so how can you deny me? **Nor do I know what will be done with me or with you, in this #world: will I be made to leave my [native] #land, or will I be #slain as was done with [some] prophets before me, or will you #stone me to death, or will the earth be made to swallow you as [it did] deniers before you?** I only follow what is revealed to me, that is, the Qur'ān, and I do not invent anything myself. And I am only a plain warner', one whose warning is plain. **(Tafsir Al Jalalayn, Commentary on Surah 46:9, Source)**

ትርጓሜውም

«..እኔ (በአምላክ የተላኩ) የመጀመሪያው መልዕክተኛ አይደለሁም፡፡ ቀደም ብለው ከኔ በፊት ብዙዎቹ መጥተዋል እንደዛ ከሆነ ታዲያ ለምን በኔ ታስተባብላላችሁ? እኔ በኔም ሆነ በናንተ እዚህች ምድር ላይ ምን እንደሚሰራ (እንደሚጋጥመን) አላውቅም፡፡ የተወለድኩበትን ሀገር ለቅቄ እሄድ ይሆን ወይንስ ከኔ በፊት እንዳለፉ (አንዳንድ) ነብያት በአሰቃቂ ሁኔታ እገደል ይሆን ወይንስ ወግረው ይገድሉኝ ይሆን ወይንስ ከናንተ በፊት እንደነበሩ ከሀድያን ምድር እናንተን (ለጥፋታችሁ)

ተሰንጥቃ ትውጣችሁ ይሆን፡፡ እኔ የምከተለው ወደ እኔ የሚወርድልኝን(ራዕይ) ቁርአንን ብቻ ነው፡፡ ከራሴ ምንም ነገር አልፈጥርም፡፡ እኔም ግልጽ አስጠንቃቂ ብቻ እንጂ ሌላ አይደለሁም፡፡» ተፍሲር አልጀላለይን ለ46፡9 የሰጡት ማብራሪያ፡፡

ኢማም ቁርጡቢ የአቡ ጀዕፈርን ንግግር ጠቅሰው እንዲህ ይላሉ፡-

لَا يَدْرِي صَلَّى اللَّه عَلَيْهِ وَسَلَّمَ مَا يَلْحَقهُ وَإِيَّاهُمْ مِنْ مَرَض وَصِحَّة وَرُخْص وَغَلَاء وَغِنًى وَفَقْر

> He (peace be upon him) doesn't know what would follow for him and them from #sickness, #health, #authority, #cheap prices, #high prices, #wealth and #poverty. **(Abu 'Abdullah Al-Qurtubi, *Tasfir al Jami' li-ahkam al-Qur'an,* Commentary on Surah 46:9, Source)**

ትርጓሜውም

« እሳቸው (ሰ.ዐ.ወ) ስለሚጋጥማቸው ነገር ምንም ነገር አያውቁም ከሚጋጥማቸው ውስጥ ህመም፣ጤንነት፣ስልጣን፣ርካሽ ዋጋ፣ውድ ዋጋ፣ ሀብት፣ጤንነት (የቱ እንደሚገጥማቸው አያውቁም፡፡

በተመሳሳይ ኢብኑ ከሲርም የኢማም ሀሰነል በስሪን ንግግር ዋቢ አድረገው ተፍሲራቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡-

أَمَّا فِي الْآخِرَة فَمَعَاذَ اللَّه وَقَدْ عَلِمَ أَنَّهُ فِي الْجَنَّة وَلَكِنْ قَالَ لَا أَدْرِي مَا يُفْعَل بِي وَلَا بِكُمْ فِي الدُّنْيَا أُخْرَجُ كَمَا أُخْرِجَتْ الْأَنْبِيَاءُ عَلَيْهِمْ الصَّلَاة وَالسَّلَام مِنْ قَبْلِي ؟ أَمْ أُقْتَلُ كَمَا قُتِلَتْ الْأَنْبِيَاء مِنْ قَبْلِي ؟

وَهَذَا الْقَوْل هُوَ الَّذِي عَوَّلَ عَلَيْهِ اِبْن جَرِير وَأَنَّهُ لَا يَجُوز غَيْره وَلَا شَكَّ أَنَّ هَذَا هُوَ اللَّائِق بِهِ صَلَّى اللَّه عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَإِنَّهُ بِالنِّسْبَةِ إِلَى الْآخِرَة جَازِم أَنَّهُ يَصِير إِلَى الْجَنَّة هُوَ وَمَنْ اِتَّبَعَهُ . وَأَمَّا فِي الدُّنْيَا فَلَمْ يَدْرِ مَا كَانَ يَئُول إِلَيْهِ أَمْره وَأَمْر مُشْرِكِي قُرَيْش إِلَى مَاذَا ؟ أَيُؤْمِنُونَ أَمْ يَكْفُرُونَ فَيُعَذَّبُونَ فَيُسْتَأْصَلُونَ بِكُفْرِهِمْ

> As for the Hereafter, I seek refuge in Allah and he (i.e. the Prophet) knew that he was going to paradise, but he said "I don't know what He (i.e. Allah) will do to me and to you in this life. Will I be kicked out just as the Prophets (may Allah bestow His peace and blessings upon them) before me were kicked out? Or would I be killed just as the Prophets before me were killed?"
>
> And this is the opinion that Ibn Jareer (i.e. Tabari) took and insisted that there should not be another opinion in this matter; for there is no doubt that this is the suitable explanation that suits the Prophet (peace be upon him). This is because in regards to the Hereafter it is certain that he (i.e. the Prophet) will go to paradise along with those who followed him. And in regards to this life, he didn't know what was going to happen to him or the polytheists of Quraysh. Were they going to believe, or disbelieve and be punished and extirpated for their disbelief? **(Tafsir Ibn Kathir, Commentary on Surah 46:9, Source)**

በአጭሩ ሲጠቃለል፡-

- ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጀነት ስለመግባታቸው የጀነትም ቁንጮ ስለመሆናቸው ጥርጥር የለውም አንቀጹም ስለዚህ አያወራም፡፡
- አንቀጹ የሚያወራው በዚህች ምድር እንደ ሰው ስሚያጋጥማቸው ክስተቶች እንደ ማያውቁ ነው የሚገልጹት እንዚህ ክስተቶች ውስጥ ከዚህ በፊት ሌሎች ነብያን ከሀገር እንዳስወጡት እሳቸውንም ከሀገራቸው ያባርሯቸው እንደሆነ ወይንም ሌሎች ነብያትን እንደገደሉ እሳቸውንም ይገድሏቸው ይሆን የሚለውን ምድር ላይ ስለሚያጋጥሙ የወደፊት የህይወት ክስተቶች አያውቁም የሚል ነው፡፡
- በሌላም በኩል አንቀጹ የሚናገረው የመካ አጋሪዎች ወደፊት ከሳቸው ጋር አምነው ወደ ጀነት ይጓዛሉን ወይንስ በማጋራታቸው ጸንተው ወደ ጀሀነብ ይነዳሉ የሚለውን አስምልክቶ ማወቅ እንደማይችሉ ነው፡፡

ምክንያም የነኝህ ነገሮች እውቀት የፈጣያችን የአላህ (ሱ.ወ) ብቻና ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ እነኝህ የወደፊቱን ክስተቶች አስመልክቶ የሰማይ መላዕክትም ቢሆን እየሱስም (ዐ.ሰ) ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቢሆኑ አላህ ከፈቀደላቸው ክስተት በቀር ማንም አያውቅም፡፡

«የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፡፡ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም፡፡

በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል፡፡ ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት

ቢኾን እንጅ፡፡ ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም

አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ቢኾን እንጅ፡፡» 6:59

ምን ያምር አገላለጽ!!!!!!!

ወላሁ አዕለም!!

እውን ቁርአን የተሟላ አይደለምን?

አንዳንድ ሚሽነሪዎች ከሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ ቁርአን የተሟላ ከሆነ ተፍሲርና ሀዲስ እርሱን ለማብራራት መጠቀም ለምን አስፈለገ ምክንያቱም ቁርአን ስለራሱ ሲገልጽ የተሟላ መሆኑን ይገልጻልና ይህ አይጋጭምን? ይሉናል::

በመጀመሪያ ደረጃ ተፍሲር ማለት በኢስላማዊ የጥናት መስክ ውስጥ ራሱን የቻለ ሰፊ የትምህርት መስክ ሲሆን በአጭሩ እራሱን ቁርአን እንዲሁም ሀዲስን መሰረት በማድረግ በሙስሊም ሊቃውንት የሚቀርቡ የቁርዐን ትንታኔ ነው::

ይህን አስመልክቶ ራሳቸው የተፍሲር መጽሀፍትን በጥልቀት በማንበብ ግንዛቤን ማጥራት ይቻላል:: አሁን ወደርዕሳችን እንለፍ::

እስኪ እንደተለመደው የቁርአን አንቀጾችን አስቀምጠን ትችቶችን እንፈትሽ::

أَفَغَيْرَ اللَّهِ أَبْتَغِي حَكَمًا وَهُوَ الَّذِي أَنزَلَ إِلَيْكُمُ الْكِتَابَ مُفَصَّلًا ۚ وَالَّذِينَ آتَيْنَاهُمُ الْكِتَابَ يَعْلَمُونَ أَنَّهُ مُنَزَّلٌ مِّن رَّبِّكَ بِالْحَقِّ ۖ فَلَا تَكُونَنَّ مِنَ الْمُمْتَرِينَ [٦:١١٤]

«እርሱ ያ መጽሐፉን የተብራራ ኾኖ ወደእናንተ ያወረደ ሲኾን «ከአላህ ሌላ ዳኛን

እፈልጋለሁን» (በላቸው):: እነዚያም መጽሐፍን የሰጠናቸው እርሱ ከጌታህ ዘንድ በእውነት

የተወረደ መኾኑን ያውቃሉ:: ከተጠራጣሪዎቹም አትኹን::» 6:114

إِنَّمَا مَثَلُ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا كَمَاءٍ أَنزَلْنَاهُ مِنَ السَّمَاءِ فَاخْتَلَطَ بِهِ نَبَاتُ الْأَرْضِ مِمَّا يَأْكُلُ النَّاسُ وَالْأَنْعَامُ حَتَّىٰ إِذَا أَخَذَتِ الْأَرْضُ زُخْرُفَهَا وَازَّيَّنَتْ وَظَنَّ أَهْلُهَا أَنَّهُمْ قَادِرُونَ عَلَيْهَا أَتَاهَا أَمْرُنَا لَيْلًا أَوْ نَهَارًا فَجَعَلْنَاهَا حَصِيدًا كَأَن لَّمْ تَغْنَ بِالْأَمْسِ ۚ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [١٠:٢٤]

«የቅርቢቱ ሕይወት ምሳሌ ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ፣ በእርሱም ሰውና እንስሳዎች

ከሚበሉት የምድር በቃይ ተቀላቅሎበት (እንደ ፋፋ) ምድርም ውበትዋን በያዘችና ባጌጠች

ጊዜ ባለቤቶችዋም በርሷ ላይ እነርሱ ቻዮች መኾናቸውን ባሰቡ ጊዜ ትእዛዛችን ሌሊት

ወይም ቀን መጥቶባት ትላንት እንዳልነበረች የታጨዱች እንዳደረግናት ብጤ ነው::

እንደዚሁም ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን::» 10:24

ضَرَبَ لَكُم مَّثَلًا مِّنْ أَنفُسِكُمْ ۖ هَل لَّكُم مِّن مَّا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُم مِّن شُرَكَاءَ فِي مَا رَزَقْنَاكُمْ فَأَنتُمْ فِيهِ سَوَاءٌ تَخَافُونَهُمْ كَخِيفَتِكُمْ أَنفُسَكُمْ ۚ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يَعْقِلُونَ [٣٠:٢٨]

«ለእናንተ ከነፍሶቻችሁ የሆነን ምሳሌ አደረገላችሁ:: (እርሱም) እጆቻችሁ ከያዟቸው (ባሮች)

ውስጥ በሰጠናችሁ ጸጋ ለእናንተ ተጋሪዎች አሏችሁን? ታዲያ እናንተና እነርሱ በእርሱ

ትከከል ናችሁን? ነፍሶቻችሁን (ብጤዎቻችሁን) እንደምትፈሩ ትፈሯቸዋላችሁን? እንደዚሁ

ለሚያስተውሉ ሕዝቦች፤ አንቀጾችን እንገልጻለን::» 30:28

ወደ መልሱ ስናልፍ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ የቁርአን አንቀጾች ሀዲስና ተፍሲርን መጠቀም አይከለክሉም:: በሁለተኛ ደረጃ አብዛኛው ሚሽነሪዎች ከላይ ያሉትን ለሀሳባቸው የሚመቻቸውን አንቀጾች ብቻ በመጥቀስ መቆምን ይፈልጋሉ:: ለዚህ ሀሳባቸው መልስ የሚሰጠውን የቁርአን አንቀጽ መጥቀስ አይፈልጉም::ግዴለም እኛ እንጥቀሰው አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-

مَّن يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللَّهَ ۖ وَمَن تَوَلَّىٰ فَمَا أَرْسَلْنَاكَ عَلَيْهِمْ حَفِيظًا [٤:٨٠]

«መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ:: ከትእዛዝም የሸሸ ሰው

(አያሳስብህ):: በእነሱ ላይ ጠባቂ አድርገን አልላክንህምና::» 4:80

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው ሙስሊሞች ነብዩ ሙሀመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንድንከተል ታዘናል:: ይህ አንቀጽም የሚገልጸው መልዕክተኛውን ስለመታዘዝ አስፈላጊነት ነው:: ስለዚህ መልዕክተኛውን መታዘዝ አላህን እንደመታዘዝ ወይንም ቁርአንን እንደመከተል ነው:: ሙስሊሞች ወደ ሀዲስ (የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግርና ተግባራት) ሲሄዱ የቁርአንን መልዕክት መተው ሳይሆን በተቃራኒው የቁርአኑን መልእክት መታዘዝ ነው:: ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) መልዕክተኛውን እንድንታዘዝ አዞናል::

ሀሳቡን ይበልጥ የሚያብራራና ለጥያቄው በቂ መልስ የሚሰጥ ሌላ የቁርአን አንቀጽ ልጨምር:-

كَمَا أَرْسَلْنَا فِيكُمْ رَسُولًا مِّنكُمْ يَتْلُو عَلَيْكُمْ آيَاتِنَا وَيُزَكِّيكُمْ وَيُعَلِّمُكُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَيُعَلِّمُكُم مَّا لَمْ تَكُونُوا تَعْلَمُونَ [٢:١٥١]

«በውስጣችሁ ከናንተው የኾነን በናንተ ላይ አንቀጾቻችንን የሚያነብላችሁና የሚያጠራችሁ፣

መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራችሁ፣ ታውቁት ያልነበራችሁትንም ነገር

የሚያሳውቃችሁ የኾነን መልክተኛ እንደላክን (ጸጋን ሞላንላችሁ)::» 2:151

ቁርአኑ እንደሚገልጽልን ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያስተምሩት የነበረው የመጽሀፉን (የቁርአኑን) መልዕክት ነው:: ስለዚህ አንድ ሙስሊም ወደ ነብዩ አስተምህሮቶች ሲሄድ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቁርአናዊ አስተምህሮ ያገኛል:: ይህ ደግሞ ከላይ እነደታዘዝነው ቁርአንን መከተል ነው:: ቁርአን በርግጥም የተሟላ ነው ምክንያም ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንድንከተልና እንድንታዘዝ አሳቸው የሚያስተምሩትም ይህንን እንደሆነ ገልጾልናልና::

ከላይ በመጀመሪያ የጠቀስኩትን የቁርዐን አንቀጽ ሰንመለከት ነብዩን መታዘዝ አላህን መታዘዝ እንደሆነ ይገልጻል:: ይህም አንድ ሙስሊም ከመልዕክተኛው አውቀትና ጥበብን አንዲሁም በተረጋገጠ ሰነድ የተላለፉ አስተምህሮዎችን ቢወስድ ልክ ከአምላክ እንደወሰደው ነው:: ምክንያቱም መልዕክተኛው ያላቸው እውቀት ጥበብና አስተምህሮ ከአምላክ የተገኘ ነውና::

ቁርዐን ስለመለኮታዊ መመሪያው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚነግሩንን መመሪያዎችና ማብራሪያዎች እንዳንቀበል አዞን ቢሆን ኖሮ አልተሟላም እንል ነበር:: ግን ስለማንኛውም የቁርአን መልዕክት ቁርአን እራሱ መልዕክተኛውን እንድናማክርና በዚያም በቂ የሆነ ማብራሪያ እንደተላለፈልን ገልጾልናል::

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنكُمْ ۖ فَإِن تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ إِن كُنتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ۚ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا [٤:٥٩]

« እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ:: መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን

ታዘዙ:: በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ

(የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት፡፡ ይህ የተሻለ

መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡» 4፡59

ቁርዐን የስልጣን ባልተቤቶችን ለምሳሌ የዕውቀት ባልተቤቶችና የሀይማኖት ሊቃውንትን እንድንታዘዝ ያዘናል፡፡ ይህም አንድ ሰው በተለያዩ ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ግልጽ ያልሆኑለት ነገሮች ቢኖሩና መረዳት የሚፈልገው ነገር ቢኖር ጉዳዩን ለሀይማኖት ሊቃውንት በመግለጽ መፍትሄ ያገኛል፡፡ ቁርአን በመቀጠልም በመካከላችን ልዩነቶች ቢኖሩ ጉዳዩን በቅድሚያ ወደ ቁርዐን በመመለስ በመቀጠልም ወደ ሀዲስ በመውሰድ ያሉትን ዝርዝርአ ስተምህሮቶች እንድንመለከት ያዛል፡፡ በዚህ የቁርዐን አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) ከቁርዐን ቀጥሎ የሀዲስን የላቀ ደረጃ ያሳየናል፡፡

ማጠቃለያ

ቁርአን ማንኛውንም ነገር የሚገልጽ የተሟላ መጽሀፍ ነው፡፡ ሀዲስና የዑለሞችን ንግግር ለማብራሪያነት መጠቀም ቁርዐንን የተሟላ ከመሆን አያግደውም፡፡ ምክንያቱም ይህንን ያዘዘው እራሱ ቁርዐን ነውና፡፡ ጥያቄ ሊሆን የሚችለው የነበረ ቁርአን እራሱ ሀዲስን መጠቀም ከልክሎ ቢሆን ኖሮ ወይንም ሀዲስን እንዳንጠቀም አዞን ቢሆን ነበር፡፡ ግን ለዚህ ጉዳይ እራሱ አላህ ትእዛዝ መመሪያውን አስተላልፎልናል ክሱ በአጭሩ ሲገመገም ይህንን ይመስላል፡፡

ወሏሁ አዕለም!!!!!!

በአሪትና በወንጌል ፍረዱ?

አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖች እነኝህን ሁለት የቁርአን አንቀጾች በመጥቀስ ቁርአን በመጽሀፍ ቅዱስ እንድንፈርድ ያዘናል ሲሉ ይደመጣሉ አንቀጾችን ከዚህ በታች በመስቀመጥ ከሳቸውን እንፈትሻለን፡፡

የመጀመሪያው አንቀጽ

« እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን

የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና

ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት

(ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ፡፡ ፍሩኝም፡፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፡፡

አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡» 5፡43
ሁለተኛው አንቀጽ

«የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፡፡ አላህም ባወረደው

የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጸኞች እነርሱ ናቸው፡፡» 5፡47

<u>መልስ</u>

ወደ መልሱ ስንገባ ሁሉንም የቁርአን አንቀጾች በአውዳቸው መመልከት ይኖርብናል፡፡ የምንፈልገውን አንቀጽ ብቻ ነጥለን መመልከት ሳይሆን ከነ ሙሉ አወዱ መመልከት መልሱን ለማግኘት ይረዳናል፡፡ ምክንያቱም ቁርአን መሰረታዊ መመሪያዎቹን አስመልክቶ ራሱን መተንተን የሚችል መለኮታዊ መጽሀፍ በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን ተግባራዊ አድረገን ወደ መልሱ ስንገባ ተውራት ማለት የቃል ትርጉም ይዘቱን ብንመለከት «መመሪያ» ወይንም «የህግ መጽሀፍ» ማለት ነው፡፡

« ከጌታው ከአስረጅ ጋር የኾነ ሰው፤ ከእርሱም (ከአላህ) የኾነ መስካሪ የሚከተለው፣ ከእርሱ

በፊትም የሙሳ መጽሐፍ መሪና እዝነት ሲኾን (የመሰከረለት) የቅርቢቱን ሕይወት

እንደሚሻው ሰው ነውን እነዚያ በእርሱ (በቁርአን) ያምናሉ፡፡ ከአሕዛቦቹም በእርሱ የሚከድ

ሰው እሳት መመለሻው ናት፡፡ ከእርሱም በመጠራጠር ውስጥ አትሁን፡፡ እርሱ ከጌታህ የሆነ

እውነት ነው፡፡ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያምኑም፡፡» ፲፡17

ይህ የህግ መጽሀፍ መመሪያነት የተሰጠው ለሙሳ(ዐ.ሰ) ህዝቦች ነበር፡፡ ኢብን ከሲር ለ46፡12 የሰጡትን ማብራሪያ መመልከት ይቻላል፡፡ ለአሁን ትውልድ መመሪያችን ይሆን ዘንድ የተሰጠን ቁርአን ነው፡፡ ቁርአን ይህን አስመልክቶ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

«(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን

ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡» 2፡185

በሌላ ቦታም

«በዚህም ቁርአን ውስጥ ከየምሳሌው ሁሉ ለሰዎች መላልሰን ገለጽን፡፡ ሰውም ከነገሩ ሁሉ

ይበልጥ ክርክረ ብዙ ነው፡፡» 18፡54

«በዚህም ቁርአን ውስጥ ለሰዎች ይገሠጹ ዘንድ ከየምሳሌው ሁሉ በእርግጥ አብራራን፡፡» 39፡27

እነኝህ ከላይ የተገለጹት አገላለጾች በጠቅላላ ለመላው የሰው ልጆች ነው፡፡ የመጽሀፉ ባልተቤቶችን ከገለጻው ውጭ አላደረገም፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ክርስተያኖች የቁርአንን «ተውራትና ኤንጅል» አገላለጽ በትክክል አይረዱትም እነኝህን መለኮታዊ መጽሀፍት ቀጥታ አሁን በእጃቸው የሚገኙት መለኮታዊ መጽሀፍት እንደሆኑ አድረገው ያስባሉ፡፡ ይህ ፈጽሞ የተሳሳተ ነው፡፡ ቁርአን በተለያየ ቦታ እንኝህ መጽሀፍት እንደተበረዙ ይገልጻል፡፡ መበረዝ ማለት ከነ አካቴው መጥፋት ማለት አይደለም፡፡ ይልቅስ ከአንቀጾቹ ውስጥ የሚሹትን ክፍል በማስወገድ በፈለጉት ሌላ ክፍል መተካት ማለት ነው፡፡ ይህንን ባህሪያቸውን አሰመልክቶ ቁርአን በተለያዩ ቦታዎች ላይ ይገልጻል ለአብነት ያህልም

1. ሱረቱል በቀራህ 79

ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው፡፡ ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው፡፡ ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢኣት) ወዮላቸው፡፡

2. ሱረቱል ኒሳዕ 44

እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት (ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ፡፡ ፍሩኝም፡፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፡፡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡

ሌሎችም በተመሳሳይ 4፤46፡- 6፡91፡-10፡93፡-11፡110፡-15፡90፡-41፡45፡-62፡5

ይህ ትእዛዝም በአጭሩ ሲገለጽ ተውራትና ወንጌልን እንደተከተሉት አሁን ደግሞ ቁርአንን ይከተሉ ምክንያቱም አሁን በእጃቸው የሚገኘው ተውራትና ወንጌል ኦሪጅናልቱን አጥቶ የሰው እጅ ገብቶበታልና የተሟሉ መለኮታዊ መጽሀፍቶች አይደሉም፡፡ ይህን አባባል ይበልጥ የሚያብራራው ፡-

«ይህ ቁርአን በእስራኤል ልጆች ላይ የእነዚያን እነርሱ በእርሱ የሚለያዩበትን አብዛኛውን

ይነግራል፡፡

እርሱም ለምእምናን መምሪያና እዝነት ነው፡፡» 27፡76-77

ይህን አስመልክቶ ኢማም ጦበራኒ ለዚህ አንቀጽ የሰጡትን ማብራሪያ ስንመለከት እንዲህ ይላሉ፡-

«እየሱስን አስመልክቶ አይሁዳውያም ክርስቲያኖችም ያሉትን ብለዋል በዚህም አምላካችን አላህ ሲገልጽ የተለያያችሁበትን ነገር እውነታውን የሚገልጸው ቁርአን ነው፡፡ ስለዚህም ተከተሉት ያዘዛችሁንም ፈጽሙ ቁርአን የሚያዛችሁ ትክክለኛውን መመሪያና እውነታ ነው፡፡» ኢብን ጀሪር አጥ ጠበሪ ጀሚኡል በያን ፊ ተእዊሊል ቁርዐን ለ27፡76 የሰጡት ማብራሪያ

እንደ መግቢያ ይህንን ከያዝን አሁን ወደ አንቀጾቹ እንመለስ፡፡ የአንቀጾቹን ታሪካዊ ዳራ (ሰበበ ኑዙል) ስንመለከት፡፡ ክስተቱ የተፈጸመው መዲና ውስጥ ሲሆን ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ ከአይሁዳውያን መካከል የሆነ ሰው ዝሙትን ፈጸመ፡፡ በአይሁዳውያን ህግ መሰረት የዚህ ሰው ቅጣቱ ተወግሮ መገደል ነው፡፡ አይሁዳውያንም ወደ አላህ መልእክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ምክር ፍለጋ ሄዱ፡፡ የአላህ መልክተኛም በተሰጣቸው ህግ እንዲፈርዱ ነገሯቸው፡፡ ነገር ግን እነሱ ይህችን ስለ መውገር ምታወራውን አንቀጽ ሊደብቋት ሞከሩ፡፡ ነገር ግን ታዋቂው የአይሁድ ሊቅ የነበረው የነብዩ ባልደረባ አብደላህ ኢብኑ ሰላም(ረ.ዐ) አንቀጹን በማሳየት አጋለጣቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን እኩይ ስራቸውን በመግለጽ ተግባራቸውን በዚህ የቁርአን አንቀጽ ነቀፈ፡፡

ቁርአን ካለው ባህርይ መካከል አል-ፋሩቅ (እውነትን ከሀሰት የሚለይ) ነው፡፡ ይህም ትክክለኛ የሆኑ መለኮታዊ መመሪያዎችን ሲያጸድቅ ከነዚህ ውጭ የሆኑትን ደግሞ ሀሰትነታቸውን አጋልጦና እውነታውን ገልጾ ያልፋል፡፡ ስለዚህም ከዚህ በፊት የነበሩ ህግጋትን ሙሰዲቂ (አረጋጋጭ) በሆነው ባህርይው ሲያጸድቅ ከዚህ ውጭ የሆኑ ሀሰት የሆኑ መመሪያዎችን ደግሞ ፉርቃን በሆነው ባህሪው ሀሰቱን አስወግዶ እውነታውን በመግለጽ ያለፉ ቀደምት መጽሀፍት የተበረዙ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

ቁርአንም ተውራትና ኢንጅል እንዲፈርዱ ሲያዝ በተበረዘው ሳይሆን በቀደመውና አሪጅናል በሆነው ቅዱስ መጽሀፋቸው ነው፡፡ ይህ ሊሆን ዘንድ ግን እውነትን ከሀሰት የሚለየውን ቁርአን ሊያምኑበት ግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም የእነኝህ መጽሀፍት አሪጅናል መልክት የሚገኘው በቁርአን ውስጥ ነውና ስለዚህም የዚህ ትውልድ ብቸኛ መመሪያና የህግ መጽሀፍት ቁርአን ነው፡፡ ስለዚህም ተንጠልጥላ የተነሳችው ክስ በቀላሉ ስትፍታታ ይህችን ትመስላለች፡፡

«ከጌታው ከአስረጅ ጋር የኾነ ሰው፤ ከእርሱም (ከአላህ) የኾነ መስካሪ የሚከተለው፣ ከእርሱ

በፊትም የሙሳ መጽሐፍ መሪና እዝነት ሲኾን (የመሰከረለት) የቅርቢቱን ሕይወት

እንደሚሻው ሰው ነውን እነዚያ በእርሱ (በቁርአን) ያምናሉ፡፡ ከአሕዛቦቹም በእርሱ የሚክድ

ሰው እሳት መመለሻው ናት፡፡» ዘ፡17

ወሏሁ አዕለም!!!

መዳን በኢስላም እንዴት ነው?

አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያን ሚሽነሪዎች ከሚያላዝኑት ክስ አንዱ እስልምና መዳንን በስራ ብቻ ያደረገ ሀይማኖት ነው አንድ ሰው በእስልምና መዳኑ የሚወሰነው በሰራው ስራ ብቻ ነው ሲሉ ይደመጣሉ፡፡

ይህ ግልጽ የሆነ መሰረት የለሽ ውንጀላ ነው ምክንያቱም እስልምና መዳንን በስራ ብቻ አልገደበውም ስራ በእምነት ሊታጀብ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ መዳን በእስልምና የሁለቱም ውጤት ነው ይህም እምነትህ ሲደመር ስራህ ማለት ነው፡፡

ቁርአን ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ይላል

‹‹በጊዜያቲ እምላለሁ ሰው ሁሉ በርግጥ ኪሳራ ውስጥ ነው እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሰሩት በውነትም አደራ የተባባበሉት በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ›› 103፡1-3

ቁርአን በግልጽ እንደሚነግረን አንድ ሰው ከኪሳራ ለመዳን እምነት ወሳኝ መሆኑንና ቀጣይ መልካም ተግባራት እንደሚያስፈልጉ ነው፡፡ ይህን ካደረግን በርግጥም መዳንን አግኝተናል እንላለን፡፡ ስለዚህም ለመዳን ከመልካም ተግባራት በተጨማሪ ማመን ወሳኝ ነጥብ ነው፡፡

ጉዳዩን ይበልጥ ያብራራልን ዘንድ ሁለት ሀዲሶችን መጥቀስ በቂ ነው

የመጀመሪው ሀዲስ፡-

አቡ ሁረይራ ባስላለፉት ሀዲስ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ

‹‹ ‹‹አንድ ሰው መልካም ተግባሩ ብቻ አያድነውም›› አሉ እርሰዎም ቢሆኑ ተብለው ተጠየቁ እሳቸውም ‹‹ አዎ እኔም ብሆን አላህ በምህረቱ ካላስገባኝ በቀር ስለዚህም መልካም ተግባራትን ሚዛናዊና ፍጹም ለሱ ሲሆን ስሩ አላህን በንጋትም በቀኑ መካከልም በምሽትም ተገዙት በሁሉም ሁኔታችሁም ሚዛናዊ ሁኑ ግባችሁን (ጀነትን) ታሳኩ ዘንድ››››

ቡኻሪ ቅጽ 76 ሀዲስ ቁጥር 470

ይህ ሀዲስ በግልጽ እንደሚያስረዳን አንድ ሰው በመልካም ተግባሩ ብቻ እምነትን ሳያካትት ግቡን ማሳካት እንደማይችል ነው፡፡ ስለዚህም ካለ እምነት ለመዳን መልካም ተግባር ብቻ በቂ አይደለም፡፡

ሁለተኛው ሀዲስ፡-

አኢሻ ባስተላለፈችው ሀዲስ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ

‹‹መልካም ተግባራትን በሚገባና ከልባችሁ ስሩ ልብ በሉ ስራችሁ ብቻውን ጀነት አያስገባችሁም አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ስራ ትንሽም ብትሆን ሰውየው ጀምሮ የፀናባት ስራ ናት››

ቡኻሪ ቅጽ 76 ሀዲስ ቁጥር 471

ይህ ሀዲስ በድጋሜ መልካም ተግባራት ብቻውን ጀነት እንደማያስገባ በግልጽ ያብራራል፡፡ እንግዲህ እነኝህን የመሳሰሉ ጭራሽ በኢስላም የማይታወቁ መሰረት የለሽ ፈጠራዎችን በማንሳት ነው ሚሽነሪዎች እምቧ ከረዩ የሚሉት፡፡ በርግጥ ትችቶቹ ሁሌም ቢሆን ውሀ የሚያነሱ አይደሉም ቢደመሩ ሚዛን የማይሞሉ ገለባች እንጂ፡፡

ወሏሁ አእለም

እውን አላህ ሰዎችን ያጠማልን?

ይህን አርዕስት በተለያዩ ክርስቲያኖች በተደጋጋሚ ሲነሳ በተመለከትኩበት ወቅት ሰፋ ያለ ምላሽ መስጠት እንዳለብኝ በማሰብ የተለያዩ መረጃዎችን ማገላበጥና መጎርጎር ጀመርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ኡስታዝ ሳዲቅ (አቡ ሀይደር) ቀድሞኝ የማያዳግም ምላሽ እንደሰጠ የተረዳሁት፡፡ ምላሾቹን ከተመከትከዋቸው በኋላ ርዕሱ ሰፊና በብዙ መንገድ መመለስ የሚችል ጥያቄ በመሆኑ ኡስታዝ በአርቲክሉ ያላካተታቸውን ነጥቦች በመምረጥ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት እንደሚኖርብኝ በማሰብ ከታች እንደሚከተለው አስቀምጨዋለሁ፡፡ መልካም ንባብ!!!

አብዛኛውን ጊዜ ሚሽነሪዎች አንዳንድ የቁርአን አንቀጾችን በመጥቀስ አላህ (ሱ.ወ) እራሱ ሰዎችን ለጥመት እንደሚዳርግ አድርገው ለማቅረብ ሲሞክሩ ይስተዋላል፡፡ዛሬ በአላህ ፍቃድ ይህንን ክስ መጋረጃውን በመገላለጥ እውነታውን ለማየት እንሞክራለን፡፡ በአጠቃላይ በሚሽነሪዎች የሚጠቀሱ የቁርአን አንቀጾች በሶስት ነጥቦች ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡

1- አላህ የሻውን ሰው እንደሚያቀና የሚገልጹ አንቀጾችን በመጥቀስ፡፡
2- የአረብኛውን ቃል "ገይ" ወይንም "ጋዋ" የሚለውን በመጥቀስ፡፡
3- አላህ የተወሰኑ ማህበረሰቦች ልቦቻቸውን አትሞባቸዋል የሚሉ አንቀጾችን መሰረት በማድረግ፡፡

በአጠቃላይ የሚጠቀሱ አንቀጾች ሲጠቃለሉ በነኝህ ክፍሎች ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡ አሁን አንድ ባንድ እያስቀመጥን ምላሻቸውን እናያለን፡፡ ከዛ በፊት ግን «ሂዳያ» ወይንም «መመራት» የሚለውን ቃል ቁርዐንን መሰረት አድርገን ፍቸውን ለማየት እንሞክራለን፡፡

1- የሂዳያ (መመራት) ትርጓሜ

ቁርአን ሂዳያን አስመልክቶ ለተወሰነ ሁኔታ በተወሰነ አገላለጽ ይጠቀመዋል፡፡ የመጀመሪያው አገላለጽ ጥቅል ሲሆን ለሁሉም ፍጥረት የተሰጠ ሂዳያ (መመራት) ነው፡፡

«قَالَ رَبُّنَا الَّذِي أَعْطَىٰ كُلَّ شَيْءٍ خَلْقَهُ ثُمَّ هَدَىٰ [٢٠:٥٠]»

«ጌታችን ያ ለፍጥረቱ ነገርን ሁሉ (የሚያስፈልገውን) የሰጠ ከዚያም የመራው ነው» አለው፡፡» 20፡50

ይህ ማለት አላህ (ሱ.ወ) ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያስፈልገውን ነገር ከሰጠው በኋላ ሂዳያን(መመራትን) የሰጠበት ነው፡፡ ይህ የሂዳያ አይነት ሁሉንም ነገር ያጠቃልላል፡- የሰው ልጅ፣ጅን፣እንስሳት፣እጽዋት ሁሉም ፍጥረታት እዚህ ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡

ሁለተኛው ሂዳያ ደግሞ ለሰው ልጆችና ለጅኖች የተሰጠ ሂዳያ ሲሆን ለሚሰሩት ስራ ተጠያቂነታቸውንም አብሮ ያካተተ ነው፡፡ ይህ ሂዳያ ለሁላችንም ተብራርቶ የቀረበልን ሲሆን የፈለገ ሰው የመቀበል ያልፈለገ ሰው ደግሞ ያለመቀበል ነጻ ምርጫ አለው፡፡

وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّاهَا [٩١:٧]

فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَاهَا [٩١:٨]

قَدْ أَفْلَحَ مَن زَكَّاهَا [٩١:٩]

وَقَدْ خَابَ مَن دَسَّاهَا [٩١:١٠]

«በነፍስም ባስተካከላትም አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት (አምላክ እምላለሁ)። (ከጎጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ። (በጎጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ።›› 91:7-10

ሶስተኛው ሂዳያ ደግሞ እውነትን ለተጠሙና ሊያገኟት ለሚሹ ሰዎች የሚሰጥ ነው። የሚሰጣቸውም በሚሰሩት መልካም ስራና የውስጥ ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ ነው።

وَالَّذِينَ اهْتَدَوْا زَادَهُمْ هُدًى وَآتَاهُمْ تَقْوَاهُمْ [٤٧:١٧]

«እነዚያም የተመሩት (አላህ) መመራትን ጨመረላቸው። (ከእሳት) መጥጠበቂያቸውንም ሰጣቸው።» 47፡17

ስለዚህ አላህ ሰዎችን አይመራም ሲል በተናጠል የሚገልጸው የሶስተኛውን ክፍል ሲሆን ይህም የማይመሩበት ምክንያት ራሳቸውን ለእውነት ክፍት ባለማድረጋቸውን ለመልካም ስራ ያላቸው ተነሳሽነት የወረደ በመሆኑ ነው። ግለሰቡ ራሱን ለለውጥ ካላነሳሳና ማንነቱን ለእውነት ዝግ ካደረገ አላህ (ሱ.ወ) አሱን የሚያስገድድበት ምንም ምክንያት የለም።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّ اللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوْمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُوا مَا بِأَنفُسِهِمْ ۗ

«...አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ኹኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም።..» 13፡11

2- አላህ የሚሻውን ይመራል የሚለው አገላለጽ ምንነት

በቁርአን ውስጥ አንዳንድ አንቀጾች አላህ (ሱ.ወ) የሚሻውን እንደሚመራና የሚሻውን እንደሚያጠም የሚገልጹ አሉ ለምሳሌ

وَمَا أَرْسَلْنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوْمِهِ لِيُبَيِّنَ لَهُمْ ۖ فَيُضِلُّ اللَّهُ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي مَن يَشَاءُ ۚ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ [١٤:٤] «

«ከመልክተኛ ማንኛውንም ለእነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም። አላህም የሚሻውን ያጠማል። የሚሻውንም ያቀናል። እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።» 14:4

አንዳንድ ሰዎች በተለይ ሚሽነሪዎች ይህን አንቀጽ በመጥቀስ አላህ ራሱ ስለሚያጠም ለሰው ልጆች ነጻምርጫ አልሰጣቸውም ሲሉ ይደመድማሉ። ይህ በጣም የተሳሳተ ትርጓሜ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው እንድን የቁርዐን አንቀጽ ሌሎች አንቀጾችንና የአገላለጽ አውዱን በሀዲስ ሳናማክል በጥራዝ ነጠቅ አንድን ብቻ ነጥለን ውሳኔ እና ድምዳሜ ላይ የምንደርስበት አይደለም። ስለዚህ ይህ አገላለጽ የሚቃኘው ከላይ በጠቀስነው መሰረት እንጅ ብቻውን ተነጥሎ አይደለም።

3- የሰው ልጅ ነጻ ምርጫ አለው።

ሌሎች የቁርአን አንቀጾች ከላየ የተሠጠውን የሚሸ ነሪዎች ድምዳሜ የሚቃወሙ ናቸው፡፡ ቁርዐን በግልጽ እንደሚነግረን አላህ (ሱ.ወ) እውነትና ውሸቱን አብራርቶ ገልጾልናል፡፡ የሰው ልጅ የመቀበልም ሆነ ያለመቀበል ነጻ ምርጫ አለው፡፡

وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّاهَا [٩١:٧]

فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَاهَا [٩١:٨]

قَدْ أَفْلَحَ مَن زَكَّاهَا [٩١:٩]

وَقَدْ خَابَ مَن دَسَّاهَا [٩١:١٠]

«በነፍስም ባስተካከላትም አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት (አምላክ እምላለሁ)፡፡ (ከጎጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡፡ (በጎጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ፡፡›› 91:7-10

በተጨማሪም

«وَقُلِ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَن شَاءَ فَلْيُؤْمِن وَمَن شَاءَ فَلْيَكْفُرْ ۚ

« «እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡....›› 18:29

4- አላህ የሚመራቸው ሰዎች

አላህ (ሱ.ወ) የሚመራቸውንና የሚያጠማቸውን ሰዎች ማንነት እንዲሁም ማን በምን ምክንያት እንደሚመራና እንደሚጠም ጭምር አብራርቶ ነግሮናል፡፡

«وَيَقُولُ الَّذِينَ كَفَرُوا لَوْلَا أُنزِلَ عَلَيْهِ آيَةٌ مِّن رَّبِّهِ ۖ قُلْ إِنَّ اللَّهَ يُضِلُّ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي إِلَيْهِ مَنْ أَنَابَ [١٣:٢٧]»

« እነዚያም የካዱት «በእርሱ ላይ ከጌታው ተዓምር ለምን አልተወረደም» ይላሉ፡፡ «አላህ የሚሻውን ያጠምማል፡፡ የተመለሰውንም ሰው ወደርሱ ይመራል» በላቸው፡፡ ›› 13:27

«وَالَّذِينَ جَاهَدُوا فِينَا لَنَهْدِيَنَّهُمْ سُبُلَنَا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ لَمَعَ الْمُحْسِنِينَ [٢٩:٦٩]»

« እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን፡፡ አላህም በእርግጥ ከበጎ ሠሪዎች ጋር ነው፡፡» 29:69

«شَرَعَ لَكُم مِّنَ الدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِ نُوحًا وَالَّذِي أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا بِهِ إِبْرَاهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰ ۖ أَنْ أَقِيمُوا الدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا فِيهِ ۚ كَبُرَ عَلَى الْمُشْرِكِينَ مَا تَدْعُوهُمْ إِلَيْهِ ۚ اللَّهُ يَجْتَبِي إِلَيْهِ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي إِلَيْهِ مَن يُنِيبُ [٤٢:١٣]»

« ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን በእርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገላችሁ፡፡ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በእርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በእርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን)፡፡ በአጋሪዎቹ ላይ ያ ወደርሱ የምትጠራቸው ነገር ከበዳቸው፡፡ አላህ የሚሻውን ሰው ወደእርሱ (እምነት) ይመርጣል፡፡ የሚመለስንም ሰው ወደርሱ ይመራል፡፡ ›› 42:13

5- የሚጠሙ ሰዎች

አላህ በተመሳሳይ የሚጠሙ ሰዎችንም ማንነት ነግሮናል፡፡

« إِنَّ اللَّهَ لَا يَسْتَحْيِي أَن يَضْرِبَ مَثَلًا مَّا بَعُوضَةً فَمَا فَوْقَهَا ۚ فَأَمَّا الَّذِينَ آمَنُوا فَيَعْلَمُونَ أَنَّهُ الْحَقُّ مِن رَّبِّهِمْ ۖ وَأَمَّا الَّذِينَ كَفَرُوا فَيَقُولُونَ مَاذَا أَرَادَ اللَّهُ بِهَٰذَا مَثَلًا ۚ يُضِلُّ بِهِ كَثِيرًا وَيَهْدِي بِهِ كَثِيرًا ۚ وَمَا يُضِلُّ بِهِ إِلَّا الْفَاسِقِينَ [٢:٢٦]

« አላህ ማንኛውንም ነገር ትንኝንም ኾነ (በትንሽነት ወይም በትልቅነት) ከበላይዋ የኾነንም ምሳሌ ለማድረግ አያፍርም፡፡ እነዚያ ያመኑትማ፤ እርሱ (ምሳሌው) ከጌታቸው (የተገኘ) እውነት መኾኑን ያውቃሉ፡፡ እነዚያም የካዱትማ «አላህ በዚህ ምንን ምሳሌ ሻ» ይላሉ፡፡ በርሱ (በምሳሌው) ብዙዎችን ያሳስታል በርሱም ብዙዎችን ያቀናል፡፡ በርሱም አመፀኞችን እንጅ ሌላን አያሳስትም፡፡ ›› 2፡26

በተመሳሳይ

« يُثَبِّتُ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا بِالْقَوْلِ الثَّابِتِ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَفِي الْآخِرَةِ ۖ وَيُضِلُّ اللَّهُ الظَّالِمِينَ ۚ وَيَفْعَلُ اللَّهُ مَا يَشَاءُ [١٤:٢٧]»

« አላህ እነዚያን ያመኑትን በቅርቢቱም ሕይወት በመጨረሻይቱም (በመቃብር) በተረጋገጠው ቃል ላይ ያረጋቸዋል፡፡ ከሓዲዎችንም አላህ ያሳስታቸዋል፡፡ አላህም የሚሻውን ይሠራል፡፡ ›› 14፡27

6- አላህ እንዴት ያጠማቸዋል

አሁን ጥያቄው አላህ እንዴት ያጠማቸዋል ታዲያ የሚል ነው፡፡ የዚህ ምክንያትም ቁርዐን ውስጥ በግልጽ ተነግሮናል፡፡

« وَمَن يُشَاقِقِ الرَّسُولَ مِن بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُ الْهُدَىٰ وَيَتَّبِعْ غَيْرَ سَبِيلِ الْمُؤْمِنِينَ نُوَلِّهِ مَا تَوَلَّىٰ وَنُصْلِهِ جَهَنَّمَ ۖ وَسَاءَتْ مَصِيرًا [٤:١١٥]»

« ቅኑም መንገድ ለእርሱ ከተገለጸ በኋላ መልክተኛውን የሚጨቃጨቅና ከምእምኖቹ መንገድ ሌላ የኾነን የሚከተል ሰው (በዚህ ዓለም) በተሾመበት (ጥመት) ላይ እንሾመዋለን፤ ገሀነምንም እናገባዋለን፡፡ መመለሻይቱም ከፋች! ›› 4፡115

ስለዚህም አላህ (ሱ.ወ) የሚያጠመው የመጣለትን እውነት አልቀበልም ብሎ የራሱን ምርጫ የያዘ ሰው ከነ ምርጫው በመተው ነው፡፡

በዚህም አላህ (ሱ.ወ) ተዓምራትን ከገለጸ፣ መመሪያውን ካወረደና ነብይም ከላከ በኋላ ይህንን አልፈልግም ብሎ ወደ መረተው መንገድ የሚሄድ ሰው አላህ የሰውየውን ምርጫ ከማጽደቅ ውጭ ሊያስገድደው አይችልም፡፡ ይህ የሱ ባህርይ ስላልሆነ፡፡ ያ ሰውም በመረጠው ምርጫ ሰበብ ለሚመጣበት ቅጣትም እራሱ ሰውየው ሀላፊነቱን ይወስዳል፡፡ በዚህም አላህ (ሱ.ወ) የሰውየውን ምርጫ ከማከበር የዘለለ ምንም አይነት ዒ-ፍትህዊ ተግባር አልሰራም፡፡

7- «ሊያጠማችሁ ሽቶ» ወይንም በአረብኛው «ዩግዊኩም» የሚለው አገላለጽ

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ኑህ ለአመጸኛ ወገኖቹ በሱረቱል ሁድ ቁጥር 34 ላይ የተናገረውን አገላለጽ በማስቀመጥ ይሞግታሉ፡፡ አንቀጹ እንዲህ ይላል፡፡

« وَلَا يَنفَعُكُمْ نُصْحِي إِنْ أَرَدتُّ أَنْ أَنصَحَ لَكُمْ إِن كَانَ اللَّهُ يُرِيدُ أَن يُغْوِيَكُمْ ۚ هُوَ رَبُّكُمْ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ [١١:٣٤]»

‹‹ «ለእናንተም ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደ ኾነ ምክሬ አይጠቅማችሁም፡፡ እርሱ ጌታችሁ ነው፡፡ ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ» (አላቸው)፡፡» ፲፡34

እንደምናየው ነብዩሏህ ኑህ እየተናገሩ ያሉት ለ950 ዓመታት ጥሪ አድርገውላቸው አሻፈረኝ ያሉና በምርጫቸው የጸኑ ወገኖቻቸውን ነበር::እነኝህ ሰዎች ሁሉንም እንዲውም ኑህ (ኢ.ሰ) ያስፈራራቸው የነበረውን የጥፋት ቅጣት ሳይቀር እንዲያመጣው በድፍረት የሚገዳደሩ ነበሩ:: እናም የአላህ (ሱ.ወ) ማጥመም ከላይ እንደገለጽነው ከነምርጫቸው መተው ነበር:: ምክንያቱም እንኝህ ሰዎች እስከመጨረሻው ድረስ ምርጫቸውን ግልጽ አድረገው ነበር:: ኑህም ይህንን ቃል የተጠቀሙት የክፋት መጨረሻው ቅኑን መንገድ ስቶ መጥፋት እንደሆነ ስለሚያውቁ ነው::

فَخَلَفَ مِن بَعْدِهِمْ خَلْفٌ أَضَاعُوا الصَّلَاةَ وَاتَّبَعُوا الشَّهَوَاتِ ۖ فَسَوْفَ يَلْقَوْنَ غَيًّا [١٩:٥٩»

«ከእነሱም በኋላ ሶላትን ያጓደሉ (የተዉ) ፍላጎቶችንም የተከተሉ መጥፎ ምትኮች ተተኩ! የገሀነምንም ሸለቆ በእርግጥ ያገኛሉ::» 19:59

ሌላ ቦታ ተመሳሳይ አገላለጽ እናገኛለን:: ሰይጣን እንዲህ ማለቱ ተገልጸዋል::

«ስለአጠመምከኝም ለእነርሱ በቀጥተኛው መንገድ ላይ በእርግጥ እቀመጥባቸዋለሁ» አለ:: 7:16

በተመሳሳይ 15:39

ነገር ግን በጣም የሚገርመው እነኝህ ከአላህ ይቅርታን የሚለምኑ የሰይጣን ንግግሮች ጥፋቱን አምኖ ነገር ግን የተጠቀመው ቃል አላህ እንዳጠመመው በመገልጽ ነበር:: ሰይጣን ለጥመቱ ምርጫው የራሱ ውሳኔ እንደነበር ግልጽ ነው:: ዛሬም መሰሎቹ ምርጫቸውን አደላድለው አላህን ሊከሱ ይጥራሉ:: ምን ሞኝነት ነው!!!!

8- አላህ ልቦችን አትሞባቸዋል የሚለው አገላለጽ

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እነኝህን አንቀጾች በመጥቀስ አላህ መጀመሪውኑ የከሀድያንን ልብ ካተመባቸው ለምን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል ሲሉ ይሞግታሉ:: እንኝ ቁንጽል የሆኑ አለመረዳቶች ጥቅል የሆነውን ይዘት ካለመረዳት የመነጨ ነው:: አላህ ልቦቻቸውን የሚያትምባቸው ሰዎች መጀመሪያውኑ ለእውነት አሻፈረኝ ብለው በምርጫቸው የጸኑና በዚህም ለለውጥ ራሳቸውን ዝግ ያደረጉ ሰዎችን ነው ወይንም በአጭሩ ከላይ እንደተመለከትነው ማለት ነው:: ለዚህም ነው አላህ ሁሌም «አላህ ልቦቻቸውን አትሞባቸዋል» የሚለውን አንቀጽ ሲጠቀም እውነታውን ላልተቀበሉና አሻፈረኝ ብለው ለጸኑ ሰዎች ብቻ እንደሆነ አብሮ አያይዞ የሚገልጸው:: ምሳሌ 2:7፣ 4፣168፣ 16፣106-109

እንኝህ ሁሉ አንቀጾች የሚገልጹት ለእውነት ራሳቸውን ዝግ አድርገው ቅኑን መንገድ በፈቃዳቸው ስላልመረጡ ሰዎች ነው::

9- ማጠቃለያ

ሲጠቃለል አላህ (ሱ.ወ) ለሰው ልጅ ከምርጫው ጋር እውነትና ሀሰቱን አብራርቶ ገልጸዋል:: ይህም በፍጥረታት ተዓምራት፣ በውስጣችን ባለው ስሜት፣ ነብያትን በመላክና መለኮታዊ መጽሀፍትን በማውረድ ጭምር ነው:: እውነታውን ለመከተል ለሚፈልግና ጥረት ለሚያደርግ ሰው አላህ ይመራዋል::ከእውነታው በተቃራኒ መቆም ለሚፈልግ አላህ ከነምርጫው ይተወዋል (4:115) :: በዚህም ምርጫውና ውሳኔው ምክንያት ፍጻሜው ታትሞ እንደጠመመ ይቀራል:: (አላህ ይጠብቀንና)

እስኪ እኛም እንጠይቅ

ክርስቲያን ሚሽነሪዎች እንደነኝህ አይነት ጥያቄዎችን ከቁርአን እየመዘዙ ሲጠይቁ ተመሳሳይ አገላለጾች መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ እራሱ መኖራቸውን ይዘነጓቸዋል:: እስኪ በማስረጃ እኛ እናስታውሳቸው::

10- እንደመጽሀፍ ቅዱስ አገላለጽ እግዚአብሄር የፈርዖንን ልብ እንዳጸናው ይገልጻል::

« እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡አለው፡-ወደ፡ግብጽ፡ስትመለስ፡በእጅኽ፡ያደረግኹትን፡ተአምራት፡ኹሉ፡

በፈርዖን፡ፊት፡ታደርገው፡ዘንድ፡ተመልከት፤እኔ፡ግን፡ልቡን፡አጸናዋለኹ፥ሕዝቡንም፡አይለቅም።» ዘጸዐት 4፡21

ተመሳሳይ አገላለጾችን ዘጸአት 7፡3፣ 10፡20፣እና 10፡27 ላይ እናገኛለን፡፡

ታዲያ ዋናውን አመጸኛ ሰው የፈርአንን ልብ እግዚአብሄር ለምን አጸና፡፡ ፈርአን አመጸኛ የሆነው እግዚብሄር ልቡን ስላጸናበት ከሆነ ፈርአን ጥፋቱ ምኑ ላይ ነው፡፡

11- እግዚአብሄር ለእስራዔል የሚያስተውሉበት ልብና የሚያዩበት ዓይን አልሰጣቸውም፡፡

በጣም የሚገርሙ አገላለጾችን ደግሞ ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡

« እግዚአብሔር፡ግን፡አስተዋይ፡ልብ፥የሚያዩ፡ዐይኖች፥የሚሰሙም፡ጉሮዎች፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡

አልሰጣቸኹም።» ዘዳግም 29፡4

« ኢሳይያስ፡ደግሞ፡-በዐይኖቻቸው፡እንዳያዩ፥በልባቸውም፡እንዳያስተውሉ፥እንዳይመለሱም፥እኔም፡

እንዳልፈውሳቸው፥ዐይኖቻቸውን፡አሳወረ፡ልባቸውንም፡አደነደነ፡ብሏልና፥ስለዚህ፡ማመን፡አቃታቸው።» ዮሀንስ 12፡39-40

« ሌላዎቹም፡ደነዘዙ፤እንዲሁም፡-ዐይኖቻቸው፡እንዳያዩ፡ጉሮዎቻቸውም፡እንዳይሰሙ፡እግዚአብሔር፡

የእንቅልፍ፡መንፈስን፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡ሰጣቸው፡ተብሎ፡ተጽፏልና።» ሮሜ 11፡8

12- የመጽሀፍ ቅዱሱ አምላክ ነብያትን ሳይቀር ሆን ብሎ መንገድ ያስታል፡፡

ብዙ ሰዎች የቁርዐኑን 7፡16 እና 15፡30 በመጥቀስ አላህ (ሱ.ወ) ሰይጣንን መንገድ እንዳሳተው በመግለጽ ለሰይጣን ጥብቅና ሲቆሙለት እናስተውላለን፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የያዙት መጽሀፍ ግን በአምላክ የተመረጡና የብዙ ሰዎች አስተማሪ የሆኑትን ነብያት ሳይቀር እግዚአብሄር ሆን ብሎ መንገድ እንደሚያስታቸው ያትታል፡፡

« አቤቱ፥ከመንገድኽ፡ለምን፡አሳትኸን፤እንዳንፈራኽም፡ልባችንን፡ለምን፡አጸናኽብን፤ስለ፡ባሪያዎችኽ፡

ስለ፡ርስትኽ፡ነገዶች፡ተመለስ።» ኢሳያስ 63፡17

« ነቢዩም፡ቢታለል፡ቃልንም፡ቢናገር፥ያንን፡ነቢይ፡ያታለልኹ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ነኝ፥እጄንም፡በርሱ፡

ላይ፡እዘረጋለኹ፡ከሕዝቤም፡ከእስራኤል፡መካከል፡አጠፋዋለኹ» ሕዝቅኤል 14፡9

ታዲያ ለምን ራስዎን ያታልላሉ እውነት አይሻልዎትም፡፡ እውነትን ይፈልጉ እየሱስ(ዐ.ሰ) እንዲህ ይላል፡-

« እውነትንም፡ታውቃላችኹ፡እውነትም፡ሐራነት፡ያወጣችኻል፡አላቸው።» ዮሀንስ 8፡32

ወሏሁ አዕለም

እውን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሀጥያትን ሰርተዋልን?

ይህንን ክስ በአብዛኛው የምንሰማው ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሀጥያት የጸዱ አለመሆናቸውንና እየሱስ (ዐ.ሰ) ግን ከሀጥያት የጸዳ መሆኑን ለማሳመን ከሚሞክሩ ሚሽነሪዎች ነው፡፡ በርግጥ እንደ ኢስላም አስተምህሮ ሁሉም ነብያት እየሱስ (ዐ.ሰ)ና ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጨምሮ ሁሎችም ነብያት ከሀጥያት የጸዱ ነበሩ፡፡ እዚህ ግባ ከማይባሉና ከሀጥያት ከማይቆጠሩ ስህተቶች በስተቀር ሀጥያት ውስጥ የሚገቡ አልነበሩም፡፡ ከዚህ በታች ሁሉንም ነጥቦች እየዘረዘርን የሚሽነሪዎችን ቅጥፈት እናጋልጣለን፡፡

1. አንዳንድ የቁርዐን አንቀጾችን ትክክለኛ ትርጓሜያቸው

فَاصْبِرْ إِنَّ وَعْدَ اللَّهِ حَقٌّ وَاسْتَغْفِرْ لِذَنبِكَ وَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ بِالْعَشِيِّ وَالْإِبْكَارِ [٤٠:٥٥]«

«(ሙሐመድ ሆይ!) ታገስም የአላህ ተስፋ እውነት ነውና፡፡ ለስህተትህም ምሕረትን ለምን፡፡ ከቀትር በኋላም በማለዳም ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው፡፡» 40፡55

فَاعْلَمْ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ وَاسْتَغْفِرْ لِذَنبِكَ وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَالْمُؤْمِنَاتِ ۗ وَاللَّهُ يَعْلَمُ مُتَقَلَّبَكُمْ وَمَثْوَاكُمْ [٤٧:١٩]

«እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ፡፡ ስለ ስህተትህም ለምእመናንንም ምሕረትን ለምን፡፡ አላህም መዘዋወሪያችሁን፣ መርጊያችሁንም ያውቃል፡፡» 47፡19

لِّيَغْفِرَ لَكَ اللَّهُ مَا تَقَدَّمَ مِن ذَنبِكَ وَمَا تَأَخَّرَ وَيُتِمَّ نِعْمَتَهُ عَلَيْكَ وَيَهْدِيَكَ صِرَاطًا مُّسْتَقِيمًا [٤٨:٢]

«አላህ ከኃጢአትህ ያለፈውንና የሚመጣውን ላንተ ሊምር ጸጋውንም ባንተ ላይ ሊሞላ ቀጥተኛውንም መንገድ ሊመራህ (ከፈተልህ) ፡፡» 48፡2

2. የመተናነስና ራስን ያለመካብ ምልክት

በእስልምና ውስጥ ለአንድ ሰው ከሚሰጠው የሞራል ትምህርት ውስጥ አንዱ ይህ ነው፡፡ሰውየው አምላኩን ለማስደሰት ጠንክሮ መስራቱና በአምልኮ መበርታቱ ከሱ የሚፈለገውን በጠቅላላ እያሟላ እንደሆነ አስቦ እንዳይኩራራና በራሱ እንዳይመጻደቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይልቅ ሰውየው ውስጡ ሊያድር የሚገባው ስሜት ከአምላኩ የሚጠበቀውን አሟልቶ አለመፈጸሙን መገንዘብ ነው፡፡ ይህም በሰራው ስራ

እንዳይመጻደቅ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም ጥፋቱን በመናዘዝ በተደጋጋሚ «አላህ ሆይ! በአንተ ጥበቃ ስር ሆኘ የሰራኋቸውን ስህተቶች ማረኝ» እያለ መማጸን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ምክንያት አላህ (ሱ.ወ) «አንተ ነብይ ሆይ! ለስህተትህም ምህረት ጠይቅ» ሲል አዘዘ፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሀዲስ በዚህ መልኩ አላህን ምህረት ይጠይቁት እንደነበር ተገልጸዋል፡፡ለምሳሌ «አላህ ሆይ! ከዚህ በፊት የሠራኋቸውን ወደ ፊትም የምሰራቸውን ስህተቶች ማረኝ! እንዲሁም በድብቅም በግልጽም የሰራሁትን ስህተቴን ማረኝ!» ቡኻሪ 5919

ይህ ማለት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በፍቃዳቸው ሀጥያት ይሰሩ ነበር ማለት አይደለም፡፡ ትክክለኛ አገላለጹ «በምድር ላይ ታላቁ የአምልኮ ሰው ቅንጣት ታክል ኩራት ሳይኖርበት ምህረትን የሚለምን ከሆነ እኛ ሀጥያተኞችማ ለዚህ ተግባር ይበልጥ ተገቦዎች ነን»፡፡ የሚል ነው፡፡ ወንጀለኛ ከመሆናችን አንጻር የበለጠ ለዚህ ተግባር መትጋት እንዳለብን ቁምነገር የሚያስጨብጠን ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ማየት የሚኖርብን የበለጠ ሀላፊነቶችን የተሸከመ ሰው መስፈርቱም ለየት እንደሚል ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥታ ከአምላክ መለኮታዊ ራዕይ የሚቀበሉ ነብይና በአምላክ የተመረጡ ግለሰብም ነበር፡፡ በጊዜያቸው ምንም ሀጥያት አልሰሩም ያም ሆኖ ግን ከመተናነሳቸውን ከአምልኳቸው ብዛት ለክብራቸው ሳይጨነቁ ዝቅበለው ምህረትን ይጠይቁ ነበር፡፡ እኔስ የሚለውን አንስቶ ራሱን እንዲፈትሽ ያደርጋል፡፡ አስተምህሮቱ ከቃላት በዘለለ እንዲህ በተግባር ሲሆን ይበልጥ ልብ ውስጥ ይሰርጻል፡፡

ከዝህም አልፎ የዚህ ሁሉ አምልኳቸውና መተናነሳቸው ምክንያት ሀዲስ ተቀምጦልን እናገኛለን፡፡
« ሙጊራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ፡- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እግራቸው እስኪያብጥ ድረስ የሌሊትን ሶላት (ስግደት) ይቆሙ ነበር፡፡ አንድ ሰውም እንዲህ አላቸው «አላህ ያለፈውንም የሚመጣውንም ወንጀል ምሮልዎት የለምን» እሳቸውም ሲመልሱ «ታዲያ አመስጋኝ ባሪያ መሆን የለብኝምን» ቡኻሪ 4459

3. ለተከታዮቻቸው አስተምህሮ ሲባል

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መተናነሳቸውን ለመግለጽና ተከታዮቻቸውም ይህን አስተምህሮ እነዲወስዱ በሚል ምህረትን ሲጠይቁ እናስተውላለን፡፡
« አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው « የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ «በአላህ እምላለሁ በቀን ከሰባ ጊዜ በላይ አላህን ምህረት እየጠየቅኩ ወደርሱ እመለሳለሁ» ቡኻሪ 5832

ሌላ ዘገባ ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ያጠናክርልናል፡፡ ይህ ተግባራቸው ለሰዎች አስተምህሮ እንደሆነ እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡-
« ኢብኑ ኡመር(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ «ሰዎች ሆይ! አላህን ምህረት ጠይቁት እኔ በቀን መቶ ጊዜ አላህን ምህረት እጠይቀዋለሁ» ሙስነድ አህመድ 17173

ከዚህ ጋር በተያያዘ ጉዳዩን ይበልጥ የሚያጠናክረው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያለፈውም የወደፊቱም ወንጀላቸው እንደተማረ የሚገልጸው የቁርዐን አንቀጽ የወረደው በ6ኛው ዓመተ ሂጅራ ሲሆን አቡ ሁረይራ የዘገበው በቀን ከ70 ጊዜ በላይ ምህረት እንደሚጠይቁ የሚገልጸውን ሀዲስ የተናገሩት ደግሞ ከ አንድ ኣመት በኋላ በ 7ኛው ኣመተ ሂጅራ ነው፡፡ ይህ የሚያረጋግጥልን የሳቸው ምህረት መጠየቅ ያለምንም ጥርጥር ለተከታዮቻቸው ዓርዓያ ለመሆንና ለማስተማር እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡

4. የተጠቀመው አረብኛ ቃል ሰፊ ትርጓሜ

በኢስፋሀኒ የተጻፈው «ሙፋረዳት ፊገሪቢል ቁርዐን» የተሰኘው መጽሀፍ «ጋፋር» የሚለውን ቃል እንዲህ ሲል ያስቀምጠዋል፡፡

«ከቆሻሻ ነገር ይጠበቅ ዘንድ መሸፈን» (1/362)

ይህን ከያዝን ታዲያ አንቀጾቹ ምን እንደሚሉ እንመልከት፡፡ አንቀጾቹ የሚያወሩት በሌላ አገላጽ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሀጥያት ይጠበቁ ዘንድ አላህን (ሱ.ወ) ይማጸኑ እንደነበር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ «ዘንብ» የሚለው ቃል አቻ የአማርኛ ትርጉሙ «ሀጥያት ወይንም ወንጀል» የሚል ሲሆን ከላይ በጠቀስነው የኢስፋሀኒ መጽሀፍ እንዲህ ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡
« ማንኛውም የሚያመጣው ውጤት ጥሩ ላልሆነ ተግባር እንጠቀመዋለን» (1/181)
ይህ የሚያረጋግጥልን ቃሉ በተጨማሪ የሚያገለግለው አንድ ሰው በጠበቀው መልኩ ላልገጠመው ማንኛውም (መልካምም ሊሆን ይችላል) ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ እሳቸውም ያልጠበቁት መልካም ያልሆነ ተግባር እንዳይገጥማቸው አላህን ይማጸኑ እንደነበሩ እንረዳለን፡፡

5. «ሀጥያት» ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ስንወስደው የነበረው ምንነት

አላህ (ሱ.ወ) በአንድ ወቅት ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) የገሰጸበት ክስተት ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

«عَبَسَ وَتَوَلَّىٰ [٨٠:١]

أَن جَاءَهُ الْأَعْمَىٰ [٨٠:٢]

وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّهُ يَزَّكَّىٰ [٨٠:٣]

أَوْ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ الذِّكْرَىٰ [٨٠:٤]

«ፊቱን አጨፈገገ፤ ዞረም፡፡ዕውሩ ስለ መጣው፡፡ምን ያሳውቅሃል? (ከነጢአቶቹ) ሊጥራራ ይከጀላል፡፡ ወይም ሊገሠጽ ግሠጼይቱም ልትጠቅመው (ይከጀላል)፡፡» 80፡1-4

ክስተቱ የተፈጸመው ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እስልምናን ያልተቀበሉ የመካ ሹማምንት ስለ እስልምና እያናገሯቸው በነበረበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረባ የነበረው ኣይነ ስውሩ አብደላህ ኢብኑ ኡሙ ሙክቱም (ረ.ዐ) ጣልቃ በመግባቱ ውይይቱ ያለፍጻሜ ተጠናቀቀ፡፡ በዚህ ጊዜ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የሱን ጣልቃ መግባት አልወደዱትም ነበር፡፡ ምክንያቱም ከእነኝህ ሰዎች መካከል አንዳቸውም እንኳን ወደ ቅኑ መንገድ ይመራሉ የሚል ተስፋ አዝለው ነበር፡፡ ከመካከላቸው(ከመካ ባላባቶች) የአንድኛቸው እንኳን ወደ ኢስላም መምጣት እየተሰቃዩ ለነበሩት እሳቸውና ባልደረቦቻቸው በትንሹም ቢሆን ስቃዩን የሚቀንስና ከለላ የሚሰጥ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ከባልደረቦቻቸው መካከል ጥያቄ ያለው ወይንም መማር የፈለገ በሌላ ሰዐት መጠየቅ እንጂ ያንን እንደ ወርቃማ የሚታይ አጋጣሚ ማደፍረስ አይገባም ነበር፡፡ ግን ባልታሰበ መልኩ የዚህ ሰሀባ ጣልቃ መግባት ውይይቱን አደፈረሰው፡፡ በርግጥ ተግባሩ ቅር የሚያሰኝ ነው፡፡ ነገር ግን በስነ ምግባር ልዕልና ለመጠቁት ነብይ ግን ይህንን እንኳ መሰማቱ ለአላህ አስደሳች

አልነበረም፡፡ ስለዚህ ተግባራቸውን ነቀፈ የሳቸው ኒያና ፍላጎት ቅን ነበር፡፡ ግን አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ እሳቸው (ሰ.ዐ.ወ) ከሚያናገሯቸው አምባገነን መሳፍንት ይልቅ ዓይነስውሩ ተወዳጅና መልካም ነበር፡፡

ይህ ሀጥያት የሚለው ቃል ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ሲደርስ ምን ያህል ደረጃው ከፍ ያለ እንደነበር ያሣያናል፡፡ እናም ሀጥያት ማለት ለሳቸው እነኝህ በመልካም ፍላጎት የተጀመሩ ግና በስህተት የተጠናቀቁ ጥቃቅን ተግባራትን ብቻ ነበሩ፡፡ (ሰለዋቱ ረቢ ወሰላሙሁ ዓለይሂ)

6. እኛ ደግሞ እንጠይቅ

የቁርዐኑ አገላለጽ በዚህ ካስቀመጥን እስኪ መጽሀፍ ቅዱስን ፈትሸን ፍጹም ሰው ብቻ ሳይሆን አምላክ ነው የሚሉት እየሱስ ምን እንደሰራ በጨረፍታ እንመልከት፡፡

እንደ ማቴወስ ገለጻ እየሱስ ሀዋርያትን ሲያስተምር እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡-

«እኛም፡ደግሞ፡የበደሉንን፡ይቅር፡እንደምንል፡በደላችንን፡ይቅር፡በለን» ማቴወስ 6፡12

በጣም የሚገርመው እዚህ አንቀጽ ላይ «በደላችንን ይቅር በለን» የሚለው ቃል የአረብኛ መጽሀፍ ቅዱስ ከፍተን ብንመለከት አቻ የአረብኛ ቃል «ወግፊር ለና ዙኑበና» የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ረሱል ሀጥያተኛ ናቸው ተብሎ የቀረቡ አንቀጾች በጠቅላላ ማለት ይቻላል የሚጠቀሙት ቃል ደግሞ ይህንኑ እራሱን ነው፡፡

በርግጥ የአንቀጹን አውድ ስንመለከተው ደቀመዛሙርቱን ለማስተማር ያዘዛቸው ቃል እንደሆነ እናያለን፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እራሱ እየሱስ ከዚህ ጸሎት ውጭ ሌላ ዓይነት አገላለጽ እነደተጠቀመ የሚገልጽ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ

«በነቢዩ፡በኢሳይያስ፡ቃል፡መጽሐፍ፡-የጌታን፡መንገድ፡አዘጋጁ፡ጥርጊያውንም፡አቅኑ፡እያለ፡በምድረ፡

በዳ፡የሚጮኽ፡ሰው፡ድምፅ፤ዐዘቅቱ፡ሸሉ፡ይሙላ፡ተራራውና፡ኰረብታውም፡ሸሉ፡ዝቅ፡

ይበል፥ጠማማውም፡የቀና፡መንገድ፡ይኹን፥ሻካራውም፡መንገድ፡ትክክል፡ይኹን፤ሥጋም፡የለበሰ፡ሸሉ፡

የእግዚአብሔርን፡ማዳን፡ይይ፡ተብሎ፡እንደ፡ተጻፈ፡ለጎጢአት፡ስርየት፡የንስሓን፡ጥምቀት፡እየሰበከ፡

በዮርዳኖስ፡ዙሪያ፡ወዳለችው፡አገር፡ሸሉ፡መጣ።» ሉቃስ 3፡3-4

በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደተገለጸው የዮሀንስ ጥምቀት የሐጥያት ስርየት ነበር፡፡ በተለያዩ ቦታዎች ደግሞ እየሱስ በዮሀንስ እንደተጠመቀ ይገልጻል፡፡ ይህ ማለት እየሱስ በዮሀንስ የሀጥያት ስርየት ጥምቀት አድርጓል ማለት ነው፡፡ ካልሆነ ጥምቀቱ ለምን አስፈለገ;

ሌላው ነጥብ

«እኔ፡ግን፡እላችኋለኹ፥በወንድሙ፡ላይ፡የሚቈጣ፡ሸሉ፡ፍርድ፡ይገባዋል፤ወንድሙንም፡ጨርቃም፡

የሚለው፡ሸሉ፡የሸንጎ፡ፍርድ፡ይገባዋል፤ደንቈሮ፡የሚለውም፡ሸሉ፡የገሃነመ፡እሳት፡ፍርድ፡ይገባዋል።» ማቴወስ 5፡22

በዚህ አንቀጽ እየሱስ እንደሚነግረን ደንቆሮ ብሎ የሚሳደብ ገሀነብ ፍርድ ይገባዋል፡፡

በሌላ ቦታ ግን እራሱ እየሱስ ይህንን ስድብ ሲጠቀም እንመለከታለን፡፡

«እናንተ፡ደንቈሮዎችና፡ዕውሮች፥ማናቸው፡ይበልጣል፤ወርቁ፡ነውን፤ወይስ፡ወርቁን፡የቀደሰው፡ቤተ፡

መቅደስ» ማቴወስ 23፡17 ተጨማሪ ሉቃስ 12፡20

ታዲያ በእየሱስ ሀጥያቱ መሰረት አላህ ይጠብቀንና የገሀነብ ፍርድ ይገባዋል ልንል ነው

ማጠቃለያ

ታዲያ እየሱስ ክርስቶስ እንደክርስቲያኖች አጠራር አምላክ የሆነውን ምህረትን ይጠይቅና ደቀመዛሙርቱም ምህረት ይለምኑት ዘንድ ያስተምር ከነበረ አምላክ ሳይሆኑ ሰው የነበሩት ታላቁ ነብይ በተግባር ይህንኑ ማስተማራቸው ልዩነቱ ምን ጋር ነው፡፡

ያምሆኖ የሰው ልጅ ለአምላኩ መተናነስና ዝቅ ዝቅ ማለት እንዳለበት እየታወቀ ነገር ግን የእየሱስ ለሀጥያት ስርየት መጠመቅና ይቅር በለኝ ማለት በእውነቱ ከአምላክ የሚጠበቅ ነውን

በተጨማሪም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዳንን አስመልክቶ የአስተምህሮታቸው መሰረት መልካም በመስራትና ምህረት በመለመን ላይ ሲሆን ይህን ይህን ማድረጋቸው አስተምህሮቱን በተግባር የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ክርስቲያኖች አገላለጽ መዳን የሚገኘው በእየሱስ መስዋዕትነት በሚገኘው «ምህረት» ነው፡፡ ታዲያ እንደ ክርስቲያኖች አገላለጽ ምህረት በዚህ ከሆነ የሚገኘው ምህረት ይጠይቁ ዘንድ ማነሳሳቱ ይበልጥ ተገቢነቱ የማን ነበር፡፡ የየትኛውስ አስተምህሮ ከሀይማኖቱ መሰረት አንጻር ስሜት ይሰጣል

ምናልባት ሚሽነሪዎች ይህችን አንቀጽ ረስተዋት ይሆናል፡-

«አንተ፡ግብዝ፥አስቀድመኽ፡ከዐይንኽ፡ምሰሶውን፡አውጣ፥ከዚያም፡በኋላ፡ከወንድምኽ፡ዐይን፡ጉድፉን፡

ታወጣ፡ዘንድ፡አጥርተኽ፡ታያለኽ።» ማቴወስ 7፡5

«እናንተ፡ዕውሮች፡መሪዎች፥ትንኝን፡የምታጠሩ፡ግመልንም፡የምትውጡ።» ማቴወስ 23፡24

ወሏሁ አዕለም!!!!

ሰይጣን ምን አጠፋ?

አንዳንድ ሚሽነሪዎች አላህ ከእኔ ውጪ ላለ ነገር አትስገዱ ብሎ ተናግሮ መልሶ እሱን ለአደም እንዴት ስገድ ይለዋል? በሌላ አነጋገር እሱ (ሰይጣን) ትክክል ነዉ ብለዉ ለርሱ ጥብቅና ይቆማሉ፡፡

መልስ፡-

******

ሰይጣን ከአጋንንት ወገን የሚቆጠር ዲያብሎስ ይባላል ፡ አጋንንቶች እና የሰዉ ልጆች ፈቃደ ልቦና (ፈሪ ዊል) የምንለዉ የተሰጣቸዉ ሲሆን መላእክት ግን በፍፁም በጌታቸዉ ላይ የማያምፁ ፍጡሮች ናቸዉ፡ሱረቱል ጂን፡ ቁጥር 14-15 ላይ ከአጋንንቱ መካከል አምላክ ላይ ያመፁ ኢ-አማንያን አሉ እነዚህ ጭፍሮች ሠይጣናት ይባላሉ ፤ ከእሰኑ ዉስጥ መሪያቸዉና ዋነኛዉ አጋንንት ‹ኢብሊስ› ወይም ዲያቢሎስ ተብሎ ይጠራል፡፡

አምልኮ ማለት ፍጡራን ለፈጣሪያቸዉ የሚያደርጉዋቸዉ የመገዛት ተግባር ነዉ ፤ አላህን መገዛት ለትእዛዛቱ ማደር ሲሆን ማመፅ ደግሞ ለኃጢአት ብሎም ለክህደት ሊዳረግ የሚችል ክፉ ስራ ነዉ፡፡ ሰይጣን በበኩሉ የሁለተኛዉን አማራጭ በመምረጥ ከአምልኮ ቀጠና በማንፈገጥ መዳረሻዉን ኃጢአት እንደ ክህደት አድርጎዋል፡፡

አሁን ወደ ዋና ጉዳዩ ስንገባ በቁርአን 2፡34 ላይ እንዲህ የሚል ነገር እንገኛለን፡-

[٢:٣٤] وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَائِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَىٰ وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ الْكَافِرِينَ

ለመላእክትም «ለአደም ስገዱ» ባልን ጊዜ (አስታውስ) ፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ ኮራም ከከሓዲዎቹም ኾነ፡፡ (34)

አሁን የሴጣን ጠበቃዎች የሚሉት ‹ከአላህ ሌላ ላለ አካል (ለአዳም) አልሰግድም በማለቱ ለምን ይወነጀላል? ሲሉም ይሞግታሉ ይህን ሃሳብ ሲሰነዝሩ ከሴጣን ጋር አብረዉ የነበሩ ወይንም አሁን ሹክ ያላቸዉ ይመስል ለሱ ‹ትክክለኛነት› ጥብቅና ይቆማሉ! ይህ ሃሳብ የሴጣንም ይሁን የነሱ እስኪ ደግሞ እራሱ የድርጊቱ ባለቤት (ሴጣን ምክንያቱን ይንገረን) ፡

18፡50 ለመላእክትም ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ (የሾነውን አስታውስ)፡፡ ወዲያውም ሰገዱ፤ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር፡፡ ከጋኔን (ነሳ) ነበር፡፡ ከጌታውም ትእዛዝ ወጣ፡፡ እርሱንና ዘሮቹን እነርሱ ለእናንተ ጠላቶች ሲኾኑ ከእኔ ላይ ረዳቶች አድርጋችሁ ትይዛላችሁን ለበዳዮች ልዋጭነቱ ከፋ! (50)

7:12 (አላህ) «ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ» አለው፡፡ «እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ፡፡ ከእሳት ፈጠርከኝ፡፡ እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው» አለ፡፡(12)

38:75 (አላህም) «ኢብሊስ ሆይ! በሁለት እጆቼ (በኃይሌ) ለፈጠርኩት ከመስገድ ምን ከለከለህ? (አሁን) ኮራህን? ወይስ (ፊቱኑ) ከትዕቢተኞቹ ነበርክ?» አለው፡፡ (75) «እኔ ከእርሱ በላጭ ነኝ፡፡ ከእሳት ፈጠርከኝ፤ ከጭቃም ፈጠርከው» አለ፡፡

17:61-62 ለመላእክትም ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ወዲያውም ሰገዱ፤ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር፡፡ «ከጭቃ ለፈጠርከው ሰው እሰግዳለሁን» አለ፡፡ (61) «ንገረኝ ይህ ያ በእኔ ላይ ያበለጥከው ነውን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስህተት በእርግጥ እስባቸዋለሁ» አለ፡፡

ከእነኝህ ቁርአን ጥቅሶች የምንረዳዉ ሴጣን የአላህን ትእዛዝ እየጣሰ መሆኑንና ይበልጥኑ ማንበብም የማይፈልጉት ነገር ሴጣን ለእምቢታዉ የሰጠዉ ምልሽን ነዉ እሱም ‹‹ እንደምን ለምበልጠዉ አዳም እተናነሳለዉ ›› የሚል እንጂ መቼ ከአንተ ዉጪ ላለ አካል አትስገድ ብለህኝ አላለም፡፡

ስለዚህ ስለዚህ ከመልሱ የምንረዳዉ ጠበቃዎቹ እንደሚሉት መስገድ የሚገባዉ ለአንተ ብቻ ነዉ እምብየዉ ሳይሆን እንዲተናነስለት በታዘዘዉ አዳም ላይ መመጻደቅ ነበር፡፡ ለዚህም ከእሳት መፈጠሩን የትልቅነት መገለጫ አድርጎ ቆጥሮ በተቃራኒዉ አዳም ከአፈር ስለተፈጠረ ዝቅ አድረገዉ እናም እኔ ለምበልጠዉ ፍጡር እንዴት ? እኮ እንዴት እራሴን ዝቅ አደረጋለዉ (በሌላ አነጋገር የፈጣሪን ትእዛዝ አሻፈረኝ አለ) በዚህም ተኮነነ እነኚህን ፀጋዎች የሰጠዉን ካልነበረበት ያስገኘዉን አካል (አላህን) ዘነጋዉ፡፡

የሚገርመዉ ከሱ በልጠዉ መገኛታቸዉ ነዉ እሱ ምክንያቱን አቅርቦዋል ደሞ እሱም አሁን ተሳስቶዋል በሉና

አዎ ለጠበቃዎቹ የምንላቸዉ ነገ የትንሳኤ ቀንም ጠበቃ የሆናችሁለት አካል እንዲህ ይላችሁዋል፡-

وَقَالَ الشَّيْطَانُ لَمَّا قُضِيَ الْأَمْرُ إِنَّ اللَّهَ وَعَدَكُمْ وَعْدَ الْحَقِّ وَوَعَدتُّكُمْ فَأَخْلَفْتُكُمْ ۖ وَمَا كَانَ لِيَ عَلَيْكُم مِّن سُلْطَانٍ إِلَّا أَن دَعَوْتُكُمْ فَاسْتَجَبْتُمْ لِي ۖ فَلَا تَلُومُونِي وَلُومُوا أَنفُسَكُم ۖ مَّا أَنَا بِمُصْرِخِكُمْ وَمَا أَنتُم بِمُصْرِخِيَّ ۖ إِنِّي كَفَرْتُ بِمَا أَشْرَكْتُمُونِ مِن قَبْلُ ۗ إِنَّ الظَّالِمِينَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ [١٤:٢٢]

ቁርአን 14:22 ነገሩም በተፈጸመ ጊዜ ሰይጣን ይላቸዋል «አላህ እውነተኛውን ቃል ኪዳን ገባላችሁ፡፡ ቃል ኪዳንም ገባሁላችሁ፤ አፈረስኩባችሁም፡፡ #ለእኔም _በእናንተ_ ላይ _ምንም_ ስልጣን አልበረኝም፡፡ ግን ጠራኋችሁ፡፡ ለእኔም ታዘዛችሁ፡፡ ስለዚህ አትውቀሱኝ፤ ነፍሶቻችሁንም ውቀሱ፡፡ እኔ የምረዳችሁ አይደለሁም፡፡ እናንተም የምትረዱኝ አይደላችሁም፡፡ እኔ ከአሁን በፊት ለአላህ ተጋሪ በአደረጋችሁት ነገር ካድኩ፡፡ በዳዮቹ ለእነርሱ በእርግጥ አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡» (22)

አላሁ አእለም (አላህ የበለጠዉን ያዉቃል)

ቁርአን የመፅሀፍ ቅዱስን አረጋጋጭ ነዉን?

መልስ፡-

******

ቁርአን መሰረታዊ የሆኑ በተለይም ከሱ (ከቁርአን) በፊት ከፈጣሪ ዘንድ የተሰጡ መጽሃፍት ጋር በተያያዘ ሶስት ባህሪያት አሉት ምናልባትም ነገሮችን ለማብራራት ያህል

1. ሙሰዲቅ፡- ከቁርአን በፊት በነበሩት መጽሐፍት ከመጥፋት ያመለጡ እዉነታዎችን ያጽድቃል /ያረጋግጣል ይህንንም በቁርአን 5፡48 እንዲህ ይነበባል፡፡
عَلَيْهِ وَمُهَيْمِنًا الْكِتَابِ مِنَ يَدَيْهِ بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا بِالْحَقِّ الْكِتَابَ إِلَيْكَ وَأَنزَلْنَا
ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ (ግድፈቱን የሚያርም) ሲኾን በእውነት አወረድን፡፡
አል -ሙሰዲቅ(አረጋጋጭ) ማለት ከርሱ በፊት የነበሩ መለኮታዊ መጽሀሐፍት የያዙትን እዉነታ የሚያጸድቅ ማለት ነዉ ፡፡ ይክርስቲያን ጸሀፊዎች ይህችን መልእክት ይመዙና ሌሎችን ባህሪያቱን በመተዉ ‹ቁርአን የመጽሐፍ‹ቅዱስ እዉነትነትን አረጋግጣEዋል››ሲሉ ጮቤ ይረግጣሉ ነገር ግን እዉነታዉ ይህ አይደልም፡፡

2. ፉርቃን፡-ይህ ሁለተኛዉ ባህሪ ነዉ ፤ይህም ማለት በቀደምት መጽሀፍት ዉስጥ የተሰገሰጉ ሀሰቶችን ከእዉነተቶቹ ለይቶና ነቅሶ የሚያወጣ ፤የሚያጋልጥ ማለት ነዉ፡፡
نَذِيرًا لِّلْعَالَمِينَ لِيَكُونَ عَبْدِهِ عَلَىٰ الْفُرْقَانَ نَزَّلَ الَّذِي تَبَارَكَ [٢٥:١]
ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት ማስጠንቀቂያ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው፡፡ ቁርአን 25፡1 ስለዚህ ቁርአን ዉሸቶችን ነቅሶ ያወጣል ማለት ነዉ፡፡

3. ሙሐይሚን፤ ይህ ባህሪዉ ደግሞ በጥንት መጽሐፍት ዉስጥ ያልተካተቱ አዳዲስ እዉነታዎችን ይገልጻል ማለት ሲሆን 5፡48 ‹‹ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ (ግድፈቱን የሚያርም) ሲኾን በእውነት አወረድን›› ‹ሙሐይሚን› የሚለዉ ቃል ተጠባባቂ ወይም ጠባቂ ተብሎ ወደ አማርኛ የተመለሰ ሲሆን ትርጉሙን በተመለከተ ሊቃዉንት እንዲህ ብለዋል፡፡

‹ሙሐይሚን› ማለት የጥንት መጽሐፍት የያዙትን እውነት ያጠቃለለና ተጨማሪ የአምላክ ፈቃዶችንና ድንቅ ስነ ምግባራትን አክሎ የያዘ ማለት ነው፡፡

‹ሙሐይሚን› በኢብኑ አባስ ትርጉም መሠረት ‹ሙእተመን› (ታማኝ)፣ ሸሂድ (መስካሪ)፣ ሐኪም (ዳኛ) የሚሉትን ትርጉሞች ሁሉ ያካትታል ኢማም ቢን ከሲር እነዚህን ሁሉ ትርጉሞች ከዘረዘሩ በኋላ እንዲህ ብለዋል፡-

የነዚህ ትርጉሞች መልእክት ተቀራራቢ ነው፡፡ ሙሐይሚን የሚለው ቃል ሁሉንም ያካትታል፡፡ ቁርአን ከርሱ በፊት ለነበሩ መለኮታዊ መጽሐፍት ታማኝ ነው፡፡ መስካሪና ዳኛም ነው፡፡ አላህ ይህን ታላቅ መጽሐፍ የመለኮታዊ መልእክቶች መቋጫ፣ እነርሱ የያዙትን መልእክት ሁሉ ያካተተ፣ የተላቀ እና ይበልጥ ምሉእ ኢድርጎታል፡፡ የቀደምት መጽሐፍትን መልካም ነገሮች ሁሉ ከመያዙም በተጨማሪ እነርሱ ያላካተቱትን ውበትና ምሉእነት አከሎለታል፡፡›

ስለዚህም ቁርአን፡-

•ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ጋር ተመሳሳይ መልእክት ሲይዝ ከመበረዝና ከመከለስ ሾልከዉ ያመለጡተ እዉነታዎችን እያጸደቀ (ሙሰዲቅ- እየሆነ ማለት ነዉ)

•ከነርሱየተለየ ወይም የሚጋጭ መልእክት ሲይዝ እዉነቱን ከሀሰት በመለየት ሀሰታቸዉን አጋልጦ እያስቀመጠ (ፉርቃን እየሆነ ማለት ነዉ)

•ከነርሱ ዉስጥ የሌለ ነገር ሲያክል ደግሞ እዉነጥን እየጨመረ ነዉ (ሙሀይሚን እየሆነ ማለት ነዉ) ይሄዳል ማለት ነዉስለዚህ ቁርአን ‹‹‹ቁርአን የመጽሐፍ‹ቅዱስ› እዉነትነትን አረጋግጣዋል› ከማለት በፊት እነዚህን መሰረታዊ መስፈርቶች በአይምሮ መያዝና መረዳት ይገባል፡፡

እውን ቁርአን ጠጅ ይፈቅዳልን?

ሚሽነሪዎች ከሚጠይቋቸው ጥያቄዎች አንዱ በቁርአን 16፡67 ጠጅ ተፈቅዶዋል ጭራሽኑ በሌላ አንቀፅ በገነትም ጠጅ እንደምትጠጡ ይናገራል ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ነው፡፡

መልስ፡-

******

ወደ መልሱ ከመግባቴ በፊት በቁርአን ዉስጥ ከመጠጥ ጋር የተያያዙ አምስት አንቀፆችን አንድ በአንድ እናያለን፡ከዚያም ከላይ ለክስ የቀረበዉን አንቀጽ አንደምታ አብረን እናያለን፡፡

አረቦች ዘንድ ነብዩ(ሰአወ) ነብይ ሆነዉ ከመላካቸዉ በፊት መጠጥ ለማህበረሰቡ እጅግ አስፈላጊ እና የዘዉትር መዝናኛቸዉ ነበር ፤በዚህም መጠጥ ቤቶች 24 ሰአት የሚሰሩበት ግዜም ነበር ቁርአን ይህን ማህበረሰብ ወደ እምንት ሲጠራ መጀመርያ መለኮታዊ ትእዛዝን የሚቀበል ‹‹ልብ›› ሳይዘጋጅ ኡድርግ/አታደርግ የሚሉ ትእዛዛት በቁርአን አልወረዱም ይህን ህብረተሰብ የማነፅ ተግባር ከተሰራ በሁዋላ እና ለፈጣሪ ትእዛዛት ዝግጁ ሲሆን ትእዛዛት ይወረዱ ጀመር ይህንንም ህብረተሰብ የሚያሳየን አንድ ሀዲስ ልጥቀስ ፡-

'Aa'ishah narrated: "The first thing that was revealed from the Qur'an was a chapter from Al-mufassal, and in it was mentioned Paradise and Hellfire. When the people embraced Islam, the verses regarding legal and illegal things were revealed. If the first thing to be revealed was: 'Do not drink intoxicants.' people would have said, 'We will never give up intoxicants." Sahih al-Bukhari 4993 Vol. 6, Book 61, Hadith 515

አኢሻ(ረአ)በዘገበችዉ ሀዲስ ሰዎች ምን ያህል ልባቸዉ ለህግ ዝግጁ እንዳልነበርና ልባቸዉን ማርጠብና ማዘገጃት አስፈላጊ እንደነበረ ያሳየናል እናም የመጀመርያዉ የቁርአን አንቀፅ መጠጥን በተመለከት የወረደዉ መካ ዉስጥ ሲሆን ይህም፡-

መጀመርያ አስካሪ መጠጥ ‹‹መልካም እንድለሆነ› ጠቆማቸዉ፡፡

ቁርአን 16:67 ከዘምባባዎችና ከወይኖችም ፍሬዎች (እንመግባችኋለን)፡፡ ከእርሱ #ጠጅንና# መልካም ምግብንም ትሠራላችሁ፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምር አልለ፡፡ (67)

ይህ አንቀፅ የሚናገረዉ ከፍሬዎች ሁለት ነገሮች እንደሚገኙ ይገልጻል፡- ለዚህም ነዉ ‹‹እና›› በሚል አያያዥ ቃል የተያያዙት

ጠጅ

መልካም ምግብ

ይህ አንቀፅ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ ነገሮች እንደሚገኝበት ተናገረ እንጂ ‹‹ጠጅ›› ጠጡ የሚል መልእክት የለዉም፤ ለሰዉ ልጅ ግን ሁለቱንም የማግኘት መብቱ የራሱ ስለሆነ ከእነዚህ ነገሮች የሚዘጋጁትን የመመርጥ ለርሱ የተተወ ነዉ፡

ይህ አንቀፅ - ጠጅ- ጥሩ ነዉ የሚል መልእክትም አላዘለም!! ስለዚህ የቁርአኑ አንቀጽ እዉነት ነዉ!! ሁለቱንም ነገሮች ሰዎች ከነዚህ ፍራፍሬዎች ያዘጋጃሉ፡ ከዚህ ነገር ‹‹መልካም የሆነ›› ነገር ከወጣ ሌላኛ የተጠቀሰዉ ነገር (ጠጅ) በተዘዋዋሪ መንገድ መልካም አይደልም ማለት ነዉ!! ይህ መልእክት በበርካታ የማህበረሰብ አባላት ጭንቅላት ዉስጥ የማሳሰብያ ደወል ደወለ ስለ አስካሪ መጠጥ ቆም ብለዉ እንዲየስቡ አደረገ ለዘመናት ይዘዉት የነበሩትን እምነትና ባህል ክፉኛ ሸረሸረ፡፡

ይህ አንቀፅ ከመጣ በሁዋላ አንዳንድ ሙስሊሞች ስለ መጠጥ ያላቸዉን ግንዛቤ ጥያቄ ዉስጥ ይፈጥርባቸዉ ጀመር እናም ከጥቂት አመታት በሁዋላ ሌላኛዉ አንቀፅ በመዲና ወረድ ይህም፡-

يَسْأَلُونَكَ عَنِ الْخَمْرِ وَالْمَيْسِرِ ۖ قُلْ فِيهِمَا إِثْمٌ كَبِيرٌ وَمَنَافِعُ لِلنَّاسِ وَإِثْمُهُمَا أَكْبَرُ مِن نَّفْعِهِمَا ۗ وَيَسْأَلُونَكَ مَاذَا يُنفِقُونَ قُلِ الْعَفْوَ ۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ اللَّهُ لَكُمُ الْآيَاتِ لَعَلَّكُمْ تَتَفَكَّرُونَ [٢:٢١٩]

ቁርአን 2፡219 አእምሮን ከሚቃወም መጠጥና ከቁማር ይጠይቁሃል፡፡ «በሁለቱም ውስጥ ታላቅ ኃጢኣትና ለሰዎች ጥቅሞች አሉባቸው፡፡ ግን ኃጢኣታቸው ከጥቅማቸው በጣም ትልቅ ነው» በላቸው፡፡ ምንን እንደሚመጽዉቱም (መጠኑን) ይጠይቁሃል፡፡ «ትርፍን (መጽውቱ)» በላቸው፡፡ እንደዚሁ ታስተነትኑ ዘንድ አላህ ለናንተ አንቀጾችን ይገልጽላችኋል፡፡ (219)

ቸርነት የቅድመ ኢስላም አረቦች ዋነኛ መገለጫ ነበር በርሱ ይፎካከሩበታል ማንነታቸዉን ይለካሉ፤ አስካሪ መጠጥ ሲጠጡ የበለጠ ቸር ስለሚሆኑ መጠጥ ጠቃሚ ነዉ የሚል እምነት ነበራቸዉ በቁማር ያገኙትንም ገንዘብ ለድሆች ስለሚሰጡም ቁማር ይጠቅማል ብለዉ ያምኑ ነበር ቁርአን የመጠጥን ክፋት ሲጠቁማቸዉ ነብዩን ስለቁማርና ስለመጠጥ ተጨማሪ ይጠይቁ ነበር ከላይ አንቀፁ ላይም ለዚህ ነዉ ‹‹ ይጠይቁሃል›› በሚል የሚጀመርዉ፡፡

ቁርአን መጠጥና ቁማር ኢምንት ጥቅም እና እጅግ የከፋ ጉዳት እንዳለባቸዉ ከገለፀ በሁዋላ ከጥቅማቸዉ ጉዳታቸዉ የሚያመዝን በመሆኑ ሲቀሩ እንደሚገባቸዉ አመላከታቸዉ ይህ መልእክት እጅግ በርካታ ሰዎችን ከመጠጥ ሱስ አላቀቀ፡፡

በዚህም አብዛኛዉ ሙስሊም መጠጥ መጠጣቱን ተዉ የተወሰኑት ደግሞ መጠጣቱን ቀነሱ ነገር ግን የተወሰኑት አሁንም አልተዉም ነበር እንደ ኡስማን ኢብን አፋን(ረአ) ያሉ ሰሃባዎች ድሮም አይጠጡም ነበር ኡስማን እንዲህ ይላሉ ‹‹ አል-ሐምር›› አእምሮን ይሰርቃል እኔ አንድንም ነገር አላየሁም ሙሉ በሙሉ ተሰረቆ ተመልሶ ወደ ነበረበት ሁኔታ የሚመለስ›› በማለት መጠጥ ምን ያህል አእምሮ ላይ ጉዳት እንደሚያደረስ ይናገራሉ፡፡

ቀጥሎም አስካሪ መጠጥ ከአምልኮ ጋር የማይሄድ ድርጊት መሆኑን ጠቆማቸዉ፡

4፡43 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንተ የሰከራችሁ ኾናችሁ የምትሉትን ነገር እስከምታውቁ የረከሳችሁም ስትኾኑ መንገድን አላፊዎች ካልኾናችሁ በስተቀር (አካላታችሁን) እስከምትታጠቡ ድረስ ስግደትን አትቅረቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም፥ ወይንም ከእናንተ አንዱ ከዓይነምድር ቢመጣ፥ ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ፣ ንጹሕ የኾነን የምድር ገጽ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይ መሓሪ ነውና፡፡ (43)

ይህ አንቀጽ አሁን ፈታኝ ሁኔታ ዉስጥ ከተታቸዉ !! በቀን 5 ግዜ ዉስጥ መስገድ አለባቸዉ ነብዩ(ሰአወ) ‹ሰላት የእምነት ምሶሶ ሰላቱን የሰገደ እምነቱን ጠብቆል የተዋት ደግሞ ትቶዋል ›› ብለዉ ተናግረዋል ስለዚህ አንድ ሙስሊም ነኝ ለሚል ሰዉ ይህንን ለመጠበቅ ከባድ

ሆኖበታል፡ምክንያቱም በቀን 5 ግዜ የሚሰገዱ ሰላቶች ለመጠጣቱ ግዜ አጥተዋል እነዚህ ሰላት ወቅቶች ሰአት እየደረሰ ስለሚያጨናግፍባቸዉ ማለት ነዉ።።

ይህ መልእክት ከፊተኛዉ በበለጠ ሁኔታ ባህላቸዉን አናወጠዉ ልምዳቸዉን ተፈታተነዉ በቀን አምስት ግዜ ያህል ለሶላት የሚሄዱ በመሆናቸዉ በነዚህ የሰላት ወቅቶች አለመጠጣት የግድ ስለሆነባቸዉ ጠዋት አይጠጡም ከዙሁር በሁዋላ ቢጠጡ የአስር ሰላት አለ።። ከአሱር በኋሊ መግሪብ፣ ከመግሪብ በኋሊ ኢሻ ሆነባቸው ስሜታቸውን ማሸነፍ የተሳናቸው ከኢሻ በኋሊ ሊጠጡ ሆነ።። በቀን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ሳይጠጡ ማሳለፍን በስሌት አለማመዳቸዉ።።

የተጠቀሱትን ጠቃሚ መልእክቶች በማዉረድ ለአመታት ስነ ልቦናቸዉን ሲያዘጋጅ ከቆየ በሁዋላ የመጨረሻዉን ቁርጥ ያለ መልእክት መጣ

ቁርአን5:90-91 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው።። (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና።። (90) ሰይጣን የሚፈልገው በሚያሰክር መጠጥና በቁማር በመካከላችሁ ጠብንና ጥላቻን ሊጥል አላህን ከማውሳትና ከስግደትም ሊያግዳችሁ ብቻ ነው።። ታዲያ እናንተ (ከእነዚህ) ተከልካዮች ናችሁን (ተከልከሉ)።። (91)

ይህ አንቀጽ ሲመጣ መዲና ዉስጥ ያሉ ሙስሊሞች ለትእዛዙ እጅ በመስጠት በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ እጅግ ድንቅ ነገረ ተከሰተ መዲና ከየቤቱ እየወጣ በሚደፋ የአስካሪ መጠጥ ጎርፍ ተጥለቀለች ሰዎች ከአፋቸዉ ዉስጥ ያስገቡትን መጠጥ እንኩዋን ሳይቀር ተፉ የማይሻር ይመስል የነበረዉ የምህበረሰብ ልምድ ተሻረ።።

ወላሁ -አእልም

ቁርአን ለምን ማርያምን የአሮን እህት ሆይ ብሎ ይጠራታል?

አብዛኛውን ጊዜ ሚሽነሪዎች ከሚያነሷቸው ክሶች መካከል «የቁርአን ደራሲዎች በሙሴ ዘመን የኖረችውን በዘጸአት 15:20 ላይ የተጠቀሰችውን የአሮንን እህት ‹‹ ሚርያምን ›› የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናት ይላሉ ምክንያቱም በቁርአን 19፡28 ላይ ‹‹የአሮን እህት ሆይ›› ብሎ የእየሱን እናት ይጠራታል>> የሚለውን ነጥብ ነው።

መልስ፡-

******

እስልምና እዉን 19፡28 ላይ የእየሱስን እናት ‹‹ የአሮን እህት ሆይ›› ብሎ የጠራት የእየሱስ እናት ማርያም እና ‹‹ ባይብል ላይ የተጠቀሰችዉ የሙሴ እህት ‹‹ነብይቱ ሚርያም›› ተመሳሰሎብን ነዉ ወይ?

በመጀመርያ በቁርአን ዉስጥ ስለ ሙሴ እህት (ሚርያም) የሚታወቅ ነገር የለም ስለዚህ ስለ ባይብልዋ ‹‹ሚርያም›› ምንም ነገር ማለት አንችልም

ሁለተኛ በነብዩ ግዜ ባይብል ወደ አረብኛ አልተተረጎመም ስለዚህ ይህን መረጃ የሚያገኙበት ዘዴ የለም ያዉም እንዲህ ሃይማኖታዊ ቀነኖ ያልሆነ እና የስም መመሳሰልን ተመርኩዞ ቁርአን ከባይብል ሲገለበጥ ‹‹ሚርያምን ›› እግለብጣለዉ ብሎ ‹‹ማርያም ›› ብሎ ገለበጠዉ ማለት አስቂኝም አሳዛኝም ክስ ነዉ።

ቁርአን ስለ ሙሳ እንዲሁም ወንድሙ አሮን ቀጥሎም ስለ እየሱስና እናቱ ማርያም #ግልፅ በሆነ መንገድ ያለቸዉን ዝምድናና በመሃከላቸዉ የዘመናት (በሙሴና/አሮን በአንድ ወገን በእየሱስ/ማርያም በሌላ ወገን) ክፍተት በግልጽ ያስቀምጥልናል።

ሙሴ እና አሮን (ዐ.ሰ) ወንድማማች ስለመሆናቸዉና በአንድ ወቅትም እንደነበሩ ከሚገልጹ በርካታ አንቀፆች

20:30 ሃሩንን ወንድሜን።

25:35 በእርግጥም ለሙሳ፣ መጽሐፍን ሰጠነው፤ ከርሱም ጋር ወንድሙን ሃሩንን ረዳት አደረግንለት።

19:53 ከችሮታችንም ወንድሙን ሃሩንን ነቢይ አድርገን ሰጠነዉ።

እየሱስ (አሰ)ከሙሴ በሁዋላ እንደመጣ ወይንም እንደተላከ የሚገልጹ የቁርአን አንቀፆች ደግሞ፡-

61:6 የመርየም ልጅ ዒሳም የ እስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልከተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልከተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ።

5:46 በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን፣ አስከተልን፤ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲሆን ሰጠነው።

2:87 ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው፡፡ #ከበኋላውም መልክተኞችን አስከታተልን፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው፡፡ በቅዱሱ መንፈስም አበረታነው፡፡ ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ ከፊሉንም ትገድላላችሁ፡፡

እነዚህ ደግሞ ስለ እየሱስ (በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ማርያም እየገለጸ እንደሆነ ልብ ይበሉ- ምክንያቱም እየሱስ የመጣዉ ከእስዋ ነዉና) ከሙሴ በሁላ ለእስራኤሎች ነብይ ሆኖ እንደተላከ ይገልፃሉ፡በተለይ 2፡87 ላይ እየሱስ (የመርየምን ልጅ) ከሙሴ በሁዋላ እንደተላከ በግልጽ ተቀምጦዋል ስለዚህ ቁርአን ስለ ሙሴ ሲያወራ እና ስለ እየሱስ ሲያወራ በመሃከላቸዉ የዘመናት እርቀት እንደነበር በገልጽ አስቀምጦዋል ማለት ይህ ማለት ደግሞ በሌላ አነጋገር (በሙሴ ወንድም አሮንና በእየሱስ እናት መርየም መካከል ይህንኑ ከፍተት እንደተጠበቀ እንደሆነ ያስረዳናል)፡፡

በተጨማሪም ስለ እየሱስን እናት መርየምን መረጃችን ለማጠናከር ሁለት ነገሮች እናቅርብ፡

አንደኛ፡-ቁርአን በርካታ ቦታ ላይ መርየምን ‹‹የኢምራን ልጅ›› እያለ ሲጠራት እናያለን ይህ ማለት ‹‹ #እንደ _እናንተ_ አረዳድ›› ከሆነ የመርየም አባት ‹‹ ኢምራን›› የአሮንም አባት መሆን አለበት! ምክንያቱም አሮን ወንድምዋ ተደርጎ ስለቀረበ ነገር ግን በባይብል መሰረት የሙሴ ፤ የአሮን እና የ‹ሚርያም› አባት ‹‹ አንበረም ›› እንጂ ‹‹ኢምራን ›› አይደልም!! (ማስረጃ አሪት ዘኁልቁ 26፡59 የእንበረም ሚስት ስም ዮካብድ ነበረ። እርስዋ በግብፅ ከሌዊ የተወለደች የሌዊ ልጅ ነበረች ለእንበረምም አሮንንና ሙሴን እኅታቸውንም #ማርያምን ወለደችለት።)

ሁለተኛ፡- እንዲሁም አሁንም በቁርአን የተገለፀችዉ መርየም (አሰ) አባትዋ ‹‹ኢምራን ነዉ (ማስረጃ 66፡12 የዒምራንን ልጅ መርየምንም ያችን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ)፡፡ በእርሱም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፍሱን፡፡ በጌታዋ ቃላትና በመጻሕፍቱም አረጋገጠች፡፡ ከታዛዦቹም ነበረች፡፡ (12)) ባይብል ግን ኢምራን ነዉ አይልም!!

ታዲያ ለምንድ ነዉ ቁርአን አሮን እህት ሆይ ብሎ የሚጠራት ፣ሀዲስስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል?

Narrated Al-Mughirah bin Shu'bah:"The Messenger of Allah (ﷺ) sent me to Najran. They said to me: 'Do you people not recite: O sister of Harun (19:28) - while between Musa and 'Eisa there is such (gap) as there is?' I did not know how to respond to them. So when I returned to the Prophet (ﷺ), I told him about that, and he said: 'Why didn't you tell them that they were named after their Prophets and righteous people before them.'" Jami` at-Tirmidhi Book 47, Hadith 3449 Vol. 5, Book 44, Hadith 3155

Mughira b. Shu'ba reported: When I came to Najran, they (the Christians of Najran) asked me: You read" O sister of Harun" (i. e. Hadrat Maryam) in the Qur'an, whereas Moses was born much before Jesus.

When I came back to Allah's Messenger (ﷺ) I asked him about that, whereupon he said: The (people of the old age) used to give names (to their persons) after the names of Apostles and pious persons who had gone before them. Sahih Muslim 2135, Book 25, Hadith 5326

ሙጊራ ቢን ሻእባን የተባለ ሰሃባ እንዲህ ሲል ዘግቦዋል ‹‹ የአላህ መልእክተኛ ወደ ነጅራኖች ዘንድ ላኩኝ ከዚያ ስደረስ ‹‹ ቁርእናችሁ መርየምን የሀሩን እህት ይላት የለምን ›› በማለት ጠየቁኝ :: አዎ አልኩዋቸዉ ‹‹ በሙሳና በኢሳ መካከል ይህን ያህል የዘመን ርቀት መኖሩንስ ታዉቁ የለምን ›› ሲሉኝ ጠየቁኝ:: ወደ አላህ መልእክተኛ በመመለስ የጠየቁኝን ነገርኩዋቸዉ :: እርሳቸዉም ‹‹አይሁዶች ልጆቻቸዉን በነብያትና በደጋግ ሰዎች ስም እንደሚጠሩ አትነግራቸዉም ነበርን ›› አሉኝ ››

ከዚህ ሀዲስ የምንረዳዉ ጥያቄዉ ድሮም የተጠየቀ እና መልስ የተሰጠበት መሆኑን ነዉ እንዲሁም ከነብዩ(ሰአወ) የምንረዳዉ በአጭሩ በ 19:28 ላይ የሃሩን እህት ሆይ ማለቱ ‹‹ የሙሳ ወንድም የነበረዉን ሃሩን ›› ስጋዊ እህት ለማለት አይደልም- እናስ - እናማ- የስም መመሳሰል ነዉ እንጂ እንዴት የእየሱስ እናትና ለሙሳ ወንድም አሮን ስጋዊ እህቱ ትሆናለች ብለህ ታስባለህ ነዉ ለምን እንደዛ አትላቸዉም ነበር ያሉትም ለዚህም ነዉ የሚገርመዉ ፤ አንድናዶች ጥያቄዉን ለጥጠዉ ‹‹ሙጊራ ›› እና ‹ የነጅራን ከርስቲያኖች ›› ስጋዊ ስለመሰላቸዉ ነዉ ! እናማ ትክክል ነበሩ የሚል አልሞት ባይ ተጋዳይ ክስ ያቀርባሉ የእኛም መልስ ‹‹ሙጊራ ›› ያልገባዉን ነብዩን ስለጠየቀ የግድ ‹‹ ስጋዊ ዝምድና ›› ለማመልከት ብሎ መደምደም መስረጃ ያስፈልጋል እንዲሁም ‹የነጅራን ከረስቲያኖች›› ደግሞ ከረስቲያን መሆናቸዉን አንርሳ የነብዩን (ሰአወ) መልእክተኝነት ለማጣጣል እና ለማብጠልጠል ያቀረቡት ክስ እንጂ እዉነትን ፍለጋ አይደልም!!

ሁለተኛዉ ነገር ከዚህ የምንረዳዉ የእየሱስ እናት ማርያም - ሃሮን - የሚባል ወንድም ሊኖራትም ይችላል መረጃዉ ባይኖረንም ስለዚህ የሃሮን እህት ሆይ ተብላ መጠራትዋ ስህተት አይሆንም:: (ማርያም

ቁርአን የሃሮን እህት ሆይ! ብሎ ሲጠራት ከብዙ ግዜ በፊት የነበረዉን ነብይ ሃሮን(የሙሳ ወንድምን) ለማመለከት ሳይሆን ከዚህ ነብይ (ከሀሮን)ግንድ የተገኘች መሆኑዋን ለመጥቀስ ነዉ:: ቁርአን ዉስጥ ተመሳሳይ ሃሳቦች ይገኛሉ:-

ምሳሌ አንድ:-

7:85 ‹‹ወደ መድየንም (ምድያን) #ወንድማቸውን #ሹዓይብን (ላከን)፤ አላቸው:- «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ:: ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም:: ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በእርግጥ መጥታላችኋለች:: ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ:: ሰዎችንም አንዳችቃቸውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉድሉባቸው:: በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ:: ይህ ምእምናን እንደኾናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው::» (85)>>

ሹአይብ ለ መድየን ህዝቦች ወንድማቸዉ እንደሆነ ይጠቅሳል ታዲያ አንድ ሰዉ ተነስቶ ሹአይብ ለእያንዳንዱ ‹‹መድየን›› ህዝብ ወንድም ነዉ ማለት አይደልም:: በተመሳሳይ መልኩ

ምሳሌ ሁለት ፡-

11:61 ላይ ‹‹ ወደ ሰሙዶችም #ወንድማቸውን #ሷሊህን (ላከን)፡፡ «ሕዝቦቼ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡ ከእርሱ ሌላ ለእናንተ አምላክ የላችሁም፡፡ እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡ ምሕረቱንም ለምኑት፡፡ ከዚህም ወደእርሱ ተመለሱ፡፡ ጌታዬ ቅርብ (ለለመነው) ተቀባይ ነውና» አላቸው፡፡ (61)>>

ሳሊህ ለሰሙድ ህዝቦች ወንድማቸዉ ላከን እያለ ይናገራል 11:61 አሁንም እነዚህ ነብዮች ለእያንዳንዱ ሰዉ ‹ሰጋዊ› ወንድሞች ናቸዉ ማለት አይደልም፡፡ ይህ የሚያሳየዉ ሰዎችን‹‹ ለመጥቀስ /ለመጥራት›› የተጠቀመበት የአነጋገር ዘይቤ ነዉ / way to address them/ በተመሳሳይ መልኩ መርየምን (የሃሮን እህት ሆይ) ሲላት ክብር ካላቸዉ ከነብያት ቤተሰብ የተገኘች መሆንዋንም በዚያዉም እየገለፀና እያፀደቀ እሱዋን ‹‹ለመጥራት/ለመጥቀስ›› የተጠቀመበት የአነጋገር ዘይቤ ነዉ፡፡ ለዚህም ስለ እስዋ ካወራ በሁዋላ ስለ አባትዋና እናትዋም ጭምር የሚነግረን መልካም ሰዎች ሆነዉ ሳለ አንቺ ከጥሩ ቤተሰብ (ከአሮን ዘር ሆነሽ አባትሽም መጥፎ ሰዉ አልነበርም እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም) ታዲያ እንዴት እኛ ሳናዉቅ ልጅ ይዘሽ ትመጭያለሽ ብለዉ እየወቀሱዋት መሆኑን ከአምዱ እንረዳለን፡፡

19:28 «የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ #መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ #እናትሽም #አመንዝራ አልነበረችም» አሏት፡፡ (28)

በመጨረሻም ባይበል ይህን አጠራር ‹‹ የሃሩን እህት ሆይ ›› የሚለዉ ባይብል ዉስጥም የተለመደ አባባል መሆኑን ተመሳሳይ አነጋገሮችም የተለመዱ መሆናቸዉን በማስረጃ እንይ፡

ነብይቱ ሚርያም - የአሮን እህት ‹‹ የአሮን እህት ሆይ ›› ተብላ ተጠርታለች (ማስረጃ ፡- ኦሪት ዘጸአት 15:20 የአሮን እኅት ነቢይቱ ማሪያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን በኋላዋ ወጡ)

የማቴዎስ ወንጌል 1:1የ#ዳዊት_ ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። (እየሱስ የዳዊት ልጅ ተብሎዋል) ግን አይደልም!!

የሉቃስ ወንጌል 3:23 ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር እንደመሰላቸው #የዮሴፍ_ ልጅ ሆኖ፥ የኤሊ ልጅ፥....>> (እዚህ ደግሞ የኢሊ ልጅ ተብሎዋል)

ኦሪት ዘፍጥረት 13:8 አብራምም ሎጥን አለው፦ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ። (አብራሃምና ሎጥ ወንድማማች ተብለዋል)

ቁርአን የሙሳ እህት ሆይ አለማለቱን ልብ በሉ ምክንያቱም ለእስራኤላዉያን የቅድስና የዘር ግንዱ በአሮን በኩል እንጂ በሙሴ አይደልም፡

ማጠቃለያ፡- ቁርአን በግልጽ ስለ ሙሳ እንዲሁም ስለ ወንድሙ አሮን በተጨማሪም ስለ እየሱስ እንዲሁም ስለ እናቱ ማርያም (ሰላም በሁሉም ላይ) ሰለ ነበራቸዉ ዝምድና አስቀምጦዋል እንዲሁም በመሃከላቸዉ የነበረዉን የግዜ ልዩነት እንዳለም ጭምር አስቀምጦዋል ፤ በስተመጨረሻም ተመሳሳይ ጥያቄ ነብዩ በህይወት በነበሩበት ግዜ እንደቀረበና ነብዩም ሰዎች ከቀደሞዋቸዉ ደጋግ ሰዎች እና ነብያት ስም መጠራት ያለ ነገረ መሆኑን ገልጽዉ መርየም (የእየሱስ እናት) የሀሮን እህት ሆይ የተባለችዉ በዚህም ምክንያት እንጂ እዉነት የስጋ ወንድመዋ አለመሆኑን በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡

ወላሁ አእለም!!

እንዴት በገነት ዉስጥ ጠጅ ይኖራል?

አንዳንድ ሰው እንዴት አስካሪ መጠጥ ገነት ውስጥ ሊኖር ይችላል ሲል ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ግን የተሳሳተ እይታ ነው ቁርዓን ጀነት ውስጥ አለ የሚለው ጠጅ ምድር ላይ ከሚገኘው ጠጅ እጅጉኑ የተለየ ነው። ስለባህርያቶቹ ከታች ጥቂት የቁርዓን አንቀጾቹን ማስቀመጡ በቂ ነው።

መልስ፡-

35:45-47 ከሚመነጭ ወይን ጠጅ በያዘ ብርጭቆ በእነርሱ ላይ ይዞርባቸዋል። (45) ነጭ ለጠጪዎች ጣፋጭ ከኾነች።(46) በእርሷ ውስጥም ምታት የለባትም። እነርሱም ከእርሷ የሚሰከሩ አይደሉም። (47)

لَّا يُصَدَّعُونَ عَنْهَا وَلَا يُنزِفُونَ [٥٦:١٩]

56:19 ከእርሷ የራስ ምታት አያገኛቸውም፤ አይሰክሩምም።(19)

مَّثَلُ الْجَنَّةِ الَّتِي وُعِدَ الْمُتَّقُونَ ۖ فِيهَا أَنْهَارٌ مِّن مَّاءٍ غَيْرِ آسِنٍ وَأَنْهَارٌ مِّن لَّبَنٍ لَّمْ يَتَغَيَّرْ طَعْمُهُ وَأَنْهَارٌ مِّنْ خَمْرٍ لَّذَّةٍ لِّلشَّارِبِينَ وَأَنْهَارٌ مِّنْ عَسَلٍ مُّصَفًّى ۖ وَلَهُمْ فِيهَا مِن كُلِّ الثَّمَرَاتِ وَمَغْفِرَةٌ مِّن رَّبِّهِمْ ۖ كَمَنْ هُوَ خَالِدٌ فِي النَّارِ وَسُقُوا مَاءً حَمِيمًا فَقَطَّعَ أَمْعَاءَهُمْ [٤٧:١٥]

47:15 የዚያች ጥንቁቆቹ ተስፋ የተሰጧት ገነት ምስል በውስጧ ሺታው ከማይለውጥ ውሃ ወንዞች፣ ጣዕሙ ከማይለወጥ ወተትም ወንዞች፣ ለጠጪዎች ሁሉ ጣፋጭ ከኾነች የወይን ጠጅም ወንዞች ከተነጠረ ማርም ወንዞች አልሉባት። ለእነርሱም በውስጧ ከፍሬዎች ሁሉ (በያይነቱ) ከጌታቸው ምሕረትም አልላቸው። (በዚች ገነት ውስጥ ዘውታሪ የኾነ ሰው) እርሱ በእሳት ውስጥ ዘውታሪ እንደኾነ ሰው፣ ሞቃትንም ውሃ እንደተጋቱ፣ አንጀቶቻቸውንም ወዲያውኑ እንደቆራረጠው ነውን? (አይደለም)። (15)

يُسْقَوْنَ مِن رَّحِيقٍ مَّخْتُومٍ [٨٣:٢٥]

خِتَامُهُ مِسْكٌ ۚ وَفِي ذَٰلِكَ فَلْيَتَنَافَسِ الْمُتَنَافِسُونَ [٨٣:٢٦]

83:25 ተጣርቶ ከታተመ ጠጅ ይጠጣሉ። ማተሚያው ምስክ ከኾነ፤

يَتَنَازَعُونَ فِيهَا كَأْسًا لَّا لَغْوٌ فِيهَا وَلَا تَأْثِيمٌ [٥٢:٢٣]

52:23በውስጧ መጠጥን ይሰጣጣሉ:: በውስጧ ውድቅ ንግግርና መውወንጀልም የለም::(23)

አጋሪዎችን ግደሉ?

አብዛኛዉን ግዜ እስልምና የጦርነት ሃይማኖት ነዉ የሰዉ ልጅን በመግደል ያዛል እየተባለ በአንደኝነት ደረጃ ከሚቀርቡ ጥያቄዎች ዉስጥ ሱረቱል ተዉባ (ምእራፍ9) ቁጥር 5 ላይ የሚገኝ አንቀፅ ነዉ።።

****

አንቀፁ እንዲህ ይነበባል፡- Quran 9፡5 « ..... የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው....» ምን ማለት ነዉ??

አንደኛ፡-

****

ይህ ጥቅስ ሁሌም ሲቀርብ ተቆርጦ ነዉ ሙሉ አንቀፁ ከስር ተቀምጦዋል ይህ የሚደረግበት ምክንያት ደግሞ የአንቀፁን አዉድ(አጠቃላይ) ሃሳብ ትንሽም ቢሆን ፍንጭ ይሰጣል ማንም ሰዉ ከላይ የሚቀረበዉን ሲያይ

«በአገኛችሁባቸዉ ስፍራ ግደሉዋቸዉ » ሲባል ትንሽ ግራ ሊገባዉ ይችላል ወደፊት በሰፊዉ እናብራራዋለን።።

ሙሉ አንቀፁ ግን ይሐዉ

فَإِذَا انسَلَخَ الْأَشْهُرُ الْحُرُمُ فَاقْتُلُوا الْمُشْرِكِينَ حَيْثُ وَجَدتُّمُوهُمْ وَخُذُوهُمْ وَاحْصُرُوهُمْ وَاقْعُدُوا لَهُمْ كُلَّ مَرْصَدٍ ۚ فَإِن تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ فَخَلُّوا سَبِيلَهُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ [٩:٥]

- 9፡5 « የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው።። ***ያዙዋቸውም፣ ከበቡዋቸውም፣ ለእነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ።። ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው።። አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።።*** ››

ሁለተኛ፡-

****

ከላይ ለመገልፅ እንደሞከርኩት ሁሌም የኢስላም ጠላቶች እስልምናን ጭራቅ አስመስሎ ለማቅረብ የሚጠቀሙት አንቀፆችን በመቆራረጥ ሲሆን በተጨማሪም ከአንቀፁ በፊትና በሁዋላ የሚመጡ ሌሎች አንቀፆችን በፍፁም አይጠቅሱም፡ ስለዚህ ለአንባቢ ይረዳዉ ዘንድ እስኪ ከ ቁጥር ነ ጀምሮ የአንቀፁን አዉድ ይዘን እስከ ቁጥር 14 አንድ በአንድ አብረን እንይ፡-

- 9:1 (ይህች) ከአላህና ከመልክተኛው ወደእነዚያ #ቃል #ኪዳን #ወደ #ተጋባችኋቸው አጋሪዎች የምትደርስ ንጽሕና ናት፡፡

ይህ በሙስሊሞች እና በጣኦት አምላኪያዉያን የሰላም ስምምነት ተደረጎ እንደነበረና ይህንንም ስምምነት አጋሪዎች በማፍረሳቸዉ ምክንያት አላህ ቃል ኪዳኑን ያፈረሱትን የአራት ወር (4 ወር) የመመለሻ ግዜ እንደሰጣቸዉ ይገልፃል ነገር ግን በዚህ ቃል ኪዳን የተገዙትን ይህ ጦርነት እንደማይመለከታቸዉ ቁጥር 4 ላይ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡፡-

- 9:4 ከአጋሪዎቹ እነዚያ #ቃል #ኪዳን የተጋባችኋቸውና ከዚያም #ምንም #ያላጎደሉባችሁ በናንተ ላይም አንድንም ያልረዱባችሁ ሲቀሩ፤ (እነዚህን) ቃል ኪዳናቸውን እስከጊዜያታቸው (መጨረሻ) ሙሉላቸው፡፡ አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና፡፡

ይህ ማለት ቃል ኪዳናቸዉን ያላፈረሱትን እንዲሁም በናንተ ላይ ያልተረዱባችሁ (ማለት፡- ከሌሎች ጋር ወግነዉ እናንተን ያልተዋጉ) ለነዚህ ሰዎች እናንተም ቃል ኪዳናቸዉን ሙሉላቸዉ ::

ስለዚህ ቁጥር 5 ላይ ሲደረስ

« የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፡፡ *ያዙዋቸውም፣ ክበቡዋቸውም፣ ለእነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ፡፡ ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና»*

ሲል ከላይ በቁጥር 4 ላይ የተጠቀሱትን አይመለከትም ይህም ማለት እስልምና ለሰላም ሁሌም ቅዲሚያ ይሰጣል ቃል ኪዳኑን አፍረስዉ ለጦርነት የተጋበዙትን ግን እጁንና እግሩን አጣምሮ ቁጭ ብለህ እይ የሚል አስተምሮ የለዉም፡፡ ስለዚህ ለእነዚያ በግዜዉ ቃል ኪዳኑን አፍረስዉ ለጦርነት የተጋበዙትን (ቃል ኪዳኑን ያፈረሱትን) እንዲዋጉዋቸዉ አዘዘ.

ሶስተኛ፡-

****

ምናልባትም ካላይ ቃል ኪዳኑን ያፈረሱት አጋሪዋች ናቸዉ ስንል መረጃ ስላላቀረብን ለዚህ ደግሞ እራሱ ቁርአኑ መልስ ይስጠናል እስኪ ቁጥር 13 ምን እንደሚል እናንብበዉ፡፡

ቁርአን 9፡13 « መሓላዎቻቸውን ያፈረሱትን መልክተኛውንም ለማውጣት ያሰቡትን ሕዝቦች #እነሱ #ለመጀመሪያ #ጊዜ #የጀመሩዋችሁ ሲኾኑ ለምን አትዋጉዋቸውም ትፈሩዋቸዋላችሁን ምእምናን እንደ ኾናችሁም አላህ ይበልጥ ልትፈሩት የተገባው ነው»

በዚህ አንቀፅ በግልፅ እንደምናየዉ እነዚህ አጋሪያን ነብዩን(ﷺ) እና በልደረቦቻቸዉን ከሀገራቸዉ ያስወጡ ሲሆኑ ጦርነቱን የጀመሩት እነሱ(አጋሪያዉያኑ) እንደሆኑ በግልፅ አስቀምጦዋል እናም አላህ በዚህ አንቀፅ ምእምናንን አትፍሩዋቸዉ ተዋጉዋቸዉ እያል ያበረታታል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጦርነት የጦርነቱ ጀማሪ ሙስሊሞች አልነበሩም፡፡ ሙስሊሞች እራሳቸዉን እየተከላከሉ እንጂ!!

አራተኛ፡-

*****

ሌላዉ ትኩርት ሊሰጠዉ የሚገባ ጉዳይ እነዚህ አጋሪያን ቃል ኪዳናቸዉን አፍረሰዉ ነብዩን (ﷺ) ከሀገር ለማዉጣት ቆርጠዉ ተነስተዉ እንዲሁም ጦርነቱን እነሱ ጀምረዉት ወደ ጦረነት ዉስጥ ተገብቶዋል እናም አንዱ ሊገልህ የነበረዉ አካል ለአንተ ጥገኝነትን ቢጠይቅ- አንተን መጋደሉን ትቶ ወደ ሰላሙ መንገድ ቢመለስ - ሙስሊሙ ወገን ላይ አንተማ ልትገለኝ መጥተህ አሁን እዚህ ቦታ ላይ(ጦር ሜዳ ላይ) ጥገኝነት መጠየቅ እራስህን ለማዳን እንጂ ለሌላ አይደልም ብሎ እንዲገለዉ ሳይሆን የታዘዘዉ የአላህ ቃል እንዲያሰማዉና እንደዉም የበለጠ ወደሰላማዊ ቦታም ጭምር እንዲያደረሰዉ ታዞዋል !! ይህ ላስተነተነዉ ድንቅ ንግግር ነዉ፡፡ የሚገረመዉ ደግሞ አጋሪዎቹ እናንተን የሚዋጉዋችሁ አለማወቃቸዉ ነዉ እንጂ የእስልምናን ዉበት ቢያዉቁ ኖሮ እንዲህ አያደረጉዋችሁም ነበር ይለናል፡፡ ስለዚህ ሙስሊሞች እራስን የመከላከል እንጂ ጦር የመምዘዝ አባዜ ተጠናዉቶአቸዉ አይደልም!!

ቁርአን 9፡6 <<ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው፡፡ ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፡፡ ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው »

አምስተኛ፡-

****

ቁርአን 9፡7

«ለአጋሪዎቹ አላህ ዘንድና እመልክተኛው ዘንድ ቃል ኪዳን እንዴት ይኖራቸዋል እነዚያ በተከበረው መስጊድ ዘንድ ቃል ኪዳን የተጋባችኋቸው ብቻ ሲቀሩ፡፡ (እነዚህ) በቃል ኪዳናቸው ለእናንተ ቀጥ እስካሉላችሁ ድረስ ለነርሱም ቀጥ በሉላቸው፡፡ አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና፡፡ **(7)** »

ከዚህ አንቀፅ ደግሞ የምንረዳቸዉ ቁምነገር አሁንም ቃል «ኪዳን የተጋባችኋቸው ብቻ ሲቀሩ » (ሰላም ወዳዶቹ) ጋር በቃል ኪዳናችን «ቀጥ» እንድንል በጥብቅ ያዘናል፡፡

ማጠቃለያ፡-

****

ስለዚህ አንቀፁ ነብዩን(ﷺ) ሲዋጉ የነበሩ ሰላም የማይፈልጉ የነበሩ አጋሪዎችን የሚመለከት እንጂ አጠቃላይ መመሪያ ሆኖ ለሁል ግዜ ሙስሊሞች ተግባራዊ የሚያደርጉት ትእዛዝ አይደልም!!

አዎ ቃል ኪዳኑን አፍርሰዉ ሙስሊሙን የተዋጉትን ሙስሊሞችም እራስን የመከላከል እርምጃ እንዲወስዱ ነገር ግን በጦርነቱ ዉስጥ ሰላም የሚፈልጉ ካሉ የአላህን ቃል እንዲሰሙ ማደረግ እና እንደዉም ወደ መጠበቂያ ቦታ እንዲያደርሱዋቸዉ ያዛል፡፡

የዚህ አይነት የጦረነት ስረአት አይደልም የዛሬ 1400 በፊት ይቅርና አሁን ሰለጠነ በሚባለዉ ግዜስ አይተንስ ሰምተን እናቃለን!! በፍፁም!! የአለም ሰላም ያሳስበናል የሚሉት ምእራባዉያንና አጫፋሪዎቻቸዉ

የሚያደረጉትን እንደሁም ያደረጉት በአይናችን እያየን ነዉ የጓንታናሞ፤ የአቡ ገሪብ ወዘተ የተፈፀሙ ግፎች ዘግናኝ እና ለአእምሮ ከባድ ነገሮች ናቸዉ።።

****ወላሁ አእለም*****